# ዜና ኢሕአፓ

ዴሞክራሲያዊ / Democratic

በኢሕአፓ የፖለቲካና የሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ
በየሶስት ወሩ እየተዘጋጀ የሚወጣ የዜና መጽሔት

ቅጽ 2 ቁጥር 1 ጥቅምት 2002 ዓ. ም.


## ርዕሰ አንቀጽ

### ድርድር ለምን? እንዴትና እስከመቼ?

መቼም ሃያአንደኛው ክፍለ-ዘመን ገና የማያሳየን ጉድ የለም። ዕድላችን ሆኖ ለሕዝብ እኩልነት፤ ለፍትሕና ለዴሞክራሲ ቆሜያለሁ እያለ የሚምልና የሚገዝት አገዛዝ ባለባት በሃገራችን በኢትዮጵያ፤ ሊያውም በሕዝብ ይሁንታ ሳይሆን በነፍጥ አስገድዶና በጎሣ ከፋፍሎ ለሚገዛ ቡድን ተዳረግንና፤ በነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ማካሄድ ሳንችል ቆይተናል።

አምባገነን ሁሌም ከሰላም የተጣላ ቢሆንም እኛ ግን ሕዝብን ከእልቂት ማዳን እንችል ዘንድ ሁሉም ዜጋ (አምባገነኑ ህወሓት/ኢሕአዴግም ጭምር) ተሳትፎ በሚያደርግበት ብሔራዊ ዕርቅ ወደ ሰላማዊ ሽግግር እንጓዝ ብለን አበክረን ታግለናል። ይህ የሰላማዊ ሽግግር አማራጭ እንደ ድክመት ተቆጥሮብን "የምን ዕርቅ ነው፡ የተጣላ ባልና ሚስት የለም" ብሎ ስርዓቱ እስኪያሾፍብን ድረስ ሳናሰልስ የሰላማዊ ሽግግርና ብሄራዊ እርቅ ወዳድነታችንን በተግባር አሳይተናል።

የደርግ አምባገነን አገዛዝ ከመውደቁ በፊት ያቀረብነው የሽግግር መንግስት አማራጭ መፍትሄ፣ የኢዴኃቅ ምሥረታና ትግል፣ የግዮን ሆቴል የሰላም ኮንፍረንስ ጥረትና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት (ኢዴኃህ) የሰላማዊ ትግል ጥረቶች ሁሉ እዚህ ላይ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። ይሁንና ማናቸውም አምባገነን ቡድን ሰላማዊ አማራጭን ለመቀበል ተፈጥሮው አይፈቅድለትምና ያለፈውም አገዛዝ በሕዝባዊ አመጽና በጠመንጃ ሃይል ወደቀ፤ እሱን የተካውም ያለ ህዝባዊ ይሁንታ በጠመንጃ ሥልጣኑን በእጁ አስገብቶ ባሽባሪነቱ ቀጠለ።

ህወሓት/ኢሕአዴግ ለሕዝብና ለሃገር ደንታ ቢስ መሆኑን እናውቃለን። የተያያዝነው ሕዝባዊ ትግል ደግሞ ግዙፍ ብሔራዊ አጀንዳ በመሆኑ ዛሬም በተገኘውና ያዋጣል በምንለው የትግል ስልት ሁሉ በመጠቀም ገዢው ቡድን የማይወደውንና የማይዋጥለትን ሰላማዊ አማራጭ እንዲቀበል ለማስገደድ በትግል ላይ ነን። ገዢው ቡድን ስልጣኑን በጠመንጃ ኃይል ማቆየት እስከቻለና የሕዝብ አመኔታ እንደሌለው እስካወቀ ድረስ ለሕዝብ

ተገኘ አይሆንም። ሰላማዊ አማራጭን የሚቀበለው በያዘው መንገድ ማለትም በግድያና በጭፍጨፋ እየገዛ መቀጠል ሲሳነውና ህልውናው ጥያቄ ላይ ሲወድቅ ብቻ ነው። ይህ ሁኔታ የሚፈጠረው አሁን ባለውና በተያዘው የትግል ስልት ብቻ ሳይሆን ገዢው ቡድን አማራጩን እንዲቀበል ሲገደድም፤ ባይቀበል ደግሞ ሊወገድም የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ስንችል ብቻ ነው። ስለዚህም ስለድርድር ስናነሳ — ድርድር ከማን፤ ለምንና መቼ? የሚሉትን ጥያቄዎች አያይዘን ማንሳት ይኖርብናል።

ቀደም አድርገን እንደገለጽነው ህወሓት/ኢሕአዴግ በግንቦት 1983 ዓ/ም በሥልጣን ላይ የተቆናጠጠው በነፃና ፍትሓዊ ምርጫ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይሁንታ አግኝቶ ሳይሆን ወደ ሥልጣን ሲጠጋ ይዞት በመጣው ነፍጡ ነው። ከሥልጣን አወጣጡ ጀምሮ ሕዝባዊ መሰረትና ድጋፍ የለውምና እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሰብዓዊ መብት፣ የእኩልነትና የፍትህ ጥያቄዎች ያስተናገደው በሃይልና በጉልበት ብቻ ነው። ገና ለስልጣን በበቃ በሁለተኛው ዓመት ማለትም እ.ኤ.አ በ1993 ዓ/ም የወቅቱ የተ.መ.ድ ዋና ፀሓፊ የነበሩት ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሌ በኤርትራና በኢትዮጵያ በአንድ ሃገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባትን ለመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ባደረጉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ገዢው ቡድን ያደረገው ጭፍጨፋ ለቀጣይ አረመኔያዊ አገዛዙ ጉልህ ምልክት ነበር።

ከጭፍጨፋና ከግድያ የማይፀዳው ይህ ቡድን በማከታተልም በአዋሳ፣ በሻምቡ፣ በበደኖ፣ በአርባጉጉ፣ በጎንደር፣ በአምቦ፣ በነቀምት፣ በጋምቤላና በሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች በጠራራ ፀሐይ ሕዝብን በጥይት ከመፍጀት አልተመለሰም። የተጨፈጨፉትና ህይወታቸው የተመሣቀለ ወገኖቻችን ቁጥርም እጅግ ከፍተኛ ሲሆን፤ ከብዛቱም የተነሳ እስካሁን ለእስር፣ ለእንግልትና ለስደት የተዳረጉትን ወገኖች ቁጥር በትክክል ማወቅ ያዳግታል።

በስመ-ምርጫ ዓመት እየቆጠሩ በሚመጡና እስካሁንም ለሦስት ጊዜ ያህል በ1987፤ በ1992 እና በ1997 ዓመተ ምህረቶች በተካሄዱና ሙሉ በሙሉም በገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ስር በዋሉት ምርጫ ተብዬዎች ሳይቀር በዚሁ ፓርቲ ቁንጮ መሪዎችም ቀጥተኛ ትዕዛዝ የተገደሉትንና ለእስርም የተዳረጉትን ወገኖቻችንንና የፈለገ-ዴሞክራሲ ሰማዕታት መቼም ቢሆን ልንዘነጋ አንችልም።

ይህ ዕውነታ ደግሞ አንዳንዶች፤ በተለይም ደግሞ የአገዛዙ ደጋፊዎችና ግብረ-በላዎች፤ እንደሚሉት በጥላቻና በጭፍን ወገንተኝነት ተጠምደን የምናራግበው ወሬ ሳይሆን ሃገር በቀልና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ጭምር በተለያዩ ጊዜያት በአሃዝና በሌሎችም በቂ ማስረጃዎች እያስደገፉ ያቀረቧቸው ዘገባዎች ያረጋገጡት ዕውነታ ነው።

ስለዚህ አሁንም በእርግጠኝነት መናገር የምንችለው ህወሓት/ኢሕአዴግ ገና ወደ ሥልጣን ሲመጣ ተላብሶ የመጣቸው ባህሪያቱ ከፉ፤ ከረፉ እንጂ መሻሻል ያልታየባቸው መሆኑን ነው። ይሁንና ህወሓት/ኢሕአዴግ በአረመኔያዊ ድርጊቶቹ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ይቅርና በዓለም ሰላም ወዳዶች ዙሪያም የሚታወቅ ቢሆንም በስሌትና በጥንቃቄ የሚጓዝ ነውና እኛም ብንሆን በጥንቃቄና በስሌት እንድንጓዝ የግድ ይላል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ፈጽሞ ልንበለጥባቸው

የማይገቡትን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የገዢውን ቡድን ዋና ዋና ባሕርያት ምንጊዜም አለመዘንጋት እጅጉን ጠቃሚ ነው እንላለን።

1ኛ. ገዢው ቡድን በገዛ ምግባሩ ደጋግሞ እንዳረጋገጠው ከፋፋይ፣ ዘረኛና አሸባሪ ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ ፀረ-ሃገራዊ አንድነትና ፀረ-ሕዝብ አገዛዝ ነው።

2ኛ. እስካሁን በገቢር ካሳያቸው ባህሪያቱ በመነሳት ገዢው ቡድን ለሥልጣኑ ማራዘሚያ ይረዳው ዘንድ ሕዝብን በጎሣ፣ በሃይማኖትና በመሰል መከፋፈያ ዘዴዎች ከመበታተን ፍላጎቱና ጥረቱ ወደሁዋላ አይልም።

3ኛ. ቅጥፈት፣ ታሪክ ማቆሸሽና የፈጠራ ታሪክን መቀፍቀፍ ዋነኛ ባሕሪያቱ ብቻ ሳይሆኑ የቡድኑ መታወቂያዎቹም ጭምር ናቸው።

4ኛ. የህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ፍጹም አምባገነን፣ ማን አለብኝና ሕገ-ወጥ ሲሆኑ ራሳቸው ላወጧቸውና ላፀደቋቸው "ሕጎች" እንኳ የሚገዙ አይደሉም።

5ኛ. ዓመት እየቆጠረ በሚመጣና ሙሉ በሙሉ በራሱ ቁጥጥር ስር በዋለ ያካባቢና ብሔራዊ በሚባሉ ስያሜዎች በሚጠሩ በራስ አዘጋጅነትና በራስ አሸናፊነት በተጠናቀቁ ምርጫ ተብዬ ሂደቶች እያጭበረበረ ለአስራ ስምንት ዓመት በጉልበት የገዛ ቡድን ነው።

6ኛ. ገዢው ቡድን ለገዛ ሃገሩ ቀናዒ ያልሆነ፤ ለሕዝብ ጨርሶ አክብሮት የሌለውና የሕዝብ የዘመናት የአንድነትና የክብሩ ምልክት የሆነውን ሰንደቅ ዓላማ ጭምር የሚያራክስና የሚያዋርድ፤ የሃገሪቱንም ዳር ድንበር በማካለል ስም የሚቸበችብ አገዛዝ መሆኑን በገዛ ምግባሩ ደጋግሞ ያረጋገጠና እያረጋገጠ ያለ አገዛዝ ነው።

ስለዚህም የምንደራደረው ከማን ጋር ነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሹ ያለጥርጥር ፀረ-ኢትዮጵያ ከሆነና የኢትዮጵያዊነትን ባህሪ ካልተላበሰ ቡድን ጋር ስለመሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ሊሆን ይገባል። ምናልባትም ይህን አቋማችንን በአክራሪነት ሊተረጉሙ የሚቃጣቸው ቢኖሩ ከዕውነቱ ዝንፍ አለማለትና "አካፋን አካፋ፤ ዶማን ዶማ" ከማለት ወደሁዋላ ላለማፈግፈግ ቃል ኪዳን እንድንገባ የግድ ይለናል።

አገርን የማዳን ታላቅ ብሔራዊ ግዴታም በዕልህ፤ በደንታ ቢስነትና በይሉኝታ ሳይሆን በጥንቃቄ፤ በብልሃትና ዕውነቱን ለሕዝብ በመንገር መደረግ ይኖርበታል እንላለን። የሰላም አማራጩ አሁን አለ ብለን አናምንም። በሂደት ከተገኘ ግን ቅድሚያ መስጠቱ ተገቢ ነው እንላለን። ይህ ጉዟችን የሚያስከፋቸው ወገኖች ባይታጡና የመከፋታቸውም ምንጭ እስከተወሰነ ደረጃ ቢገባንም፤ የትግሉን መራራነትና እልህ አስጨራሽነት ከግንዛቤ በማስገባትና ይህንንም ዕውነታ ተቀብሎ በትግሉ መርዘም ተስፋ አለመቁረጥን፤ ይልቁንም በቁርጠኝነት እስከድል መታገልን አማራጭ-የለሽ ግዴታ እንደሆነ አበክረን መምከር ይኖርብናል።

ለፍትህና ለዴሞክራሲ የምናደርገው ትግል ብዙ ውጣ-ውረዶችና የትግል አማራጮችም እንዳሉት አጥብቀን እናምናለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት አምባገነኖችን ሲሸከም የኖረበት ትከሻው ጎብጧልና ለጥገናዊ ሳይሆን ለስር-ነቀል፤ ለወቅታዊ ሳይሆን ለዘላቂ ለውጥ በጋራ መነሳት የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ስለሆነ ለተግባራዊነቱም በጋራ መነሳት አለብን እንላለን።

ካሁን በሁዋላም የተያዘው ድርድርም ሆነ ከዚህ ባሻገር የሚኖረውና ሊኖር የሚገባው

ቀጣይ ትግል ማተኮር ያለበት በ97ቱ የምርጫ ወቅት ሕዝቡ ባነሳቸውና ትግሉም ባተኮረባቸው የነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ቅድመ-ሁኔታዎች በቅድሚያ በማሟላትና እንዲሟሉም አምባገነኑን ቡድን በማስገድድ ላይ ሊሆን ይገባል።

በሃገራችን ውስጥ እግራቸውን ተክለው ከሚንቀሳቀሱ ወገኖች በኩል መጪውን ምርጫ አስመልክቶ ሰሞኑን ከሚደመጡት ዜናዎች አንዱና ዋነኛው "የምንደራደረው ለይስሙላ ምርጫ አይደለም" የሚለው የፖለቲካ መርህና ለውጥ አመላካች አቋም ተስፋ ሰጪም ነው እንላለን። ይህ ለሕዝብ የተስፋ ጭላንጭል የሰጠ አቋም መልሶ ሳይጨልም እያበራ እንዲቀጥል ማድረግና የኢትዮጵያ ሕዝብም ይህንን ተስፋ በተግባር ማየት እንዲችል ለማድረግ የተቃዋሚው ጎራ ሁሉ በዚህ ዙሪያ ትብብርና ርብርብ ማድረግ ይጠበቅበታል።

በዚህ ድርድር ሂደት ውስጥም ተቃዋሚው ጎራ በአንድነት መጓዝ ካልቻለ ተጠቃሚው ህወሓት/ኢሕአዴግ ብቻ ነውና ለአገዛዙ የነጣጠለህ ምታው በትር በቀጣይነት መመቻቸትን ስለሚያስከትል ከዚህ የፖለቲካ አረንቋ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መላቀቅ የሚቻለው የአንድነትና የህብረት ጉዞ ሲደረግ ብቻ ነው እንላለን። ከተሳካም ላለፉት 18 ዓመታት በህወሃት/ኢሕአዴግ ገዢ ቡድን የተጠቃው ተቃዋሚው ወገንና ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንድ ላይ በመሆኑ ዳግም በተናጠል ቆሞ ለጥቃት ላለመጋለጥ በሕብረት መንቀሳቀስና የውጭና የውስጥ እያሉና መሰል ከፋፋይ የብተና ዘዴዎችን እየተጠቀሙ አንድነታችንን ለሚንዱ ወገኖች ቀዳዳ መስጠት አይገባንም። በጋራ ለመንቀሳቀስ ቁርጠኛ ውሳኔ ላይ መደረስ ያለበትም ዛሬ እንጂ ነገ ለቀጣይ አደጋ ከተመቻቹ በሁዋላ ሊሆን እንደማይችል ማመን ይኖርብናል።

በሕብረት ስለመቆምና በጋራ መቀናጀት ስለሚኖርበት የፖለቲካ ድርድር ወይም ትግል መስበክና ይህንኑ ተግባራዊ ማድረግ ለየቅል ናቸው። ባለፉት ሦስት አሥርት ዓመታት ለህብረት፤ ስለህብረት ስንል የወጣናቸውና የወረድናቸውን አቀበቶችና ቁልቁለቶች ቆም ብለን ስንገመግም፤ ለአገዛዙ ቀጣይ ህይወት የሰጡና እኛንም ተቃዋሚዎችን ያሽመደመዱ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ግድፈቶችና ድክመቶች እንደነበሩን፤ ዛሬም እንዳሉን አምነን በመቀበል እነዚህን ለማስወገድ መታገል ይኖርብናል። ከውጣ-ውረዱ የቀሰምናቸውንም ብርቱ ጎኖቻችንን ማዳበርና እነዚህንም በመጠቀም ለህብረት ምሥረታ ልናውላቸው ይገባል እንላለን። ከነዚያ ያለፉ አድካሚ አቀበቶች ጉዞ ገና ብዙ መማር ይጠበቅብናል።

የረጅም ዓመታት ተከታታይ የግፍና የመከራ ገፈት ቀማሽ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብም መሸከም ከሚችለው በላይ ከደረሰበትና እየደረሰበት ከሚገኘው ግፍና መከራ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊገላገል ይገባል። ስለሆነም ነው ደግመን ደጋግመን ለድርድርም ሆነ ለቀጣዩ ትግል በጋራና በህብረት መቆም የግድ ነው የምንለው። ትግሉም የጋራ፤ ድሉም የጋራ መሆኑ የጋራ ዕምነታችን መሆንም ይኖርበታል።

............//............

## የተቃዋሚው ሚና በመጪው 2002 ዓ/ም "ምርጫ"

**(አዳሙ አበበ)**

"ታሪክ መስታወት ነው" ያለው ሊቅ ስም ጠፋኝ። አዎን! ታሪክ የትናንት ማንነት ማንፀሪያና ጉልበትና ዕውቀት ባጠጠ ጊዜም ሊመነዘር የሚችል ሃብት ነው። መቼም ታሪክ መሥራትን እንጂ በታሪክ በመኩራት በተለይ ከዘመናዊው ትውልድ የሚስተካከል

ይኖራል ለማለት ይቸግራል። ሆኖ መገኘት እንጂ ያቃተው የሆነውን በሰላ ምላስ በማወራረድ ረገድ አዲሱን ትውልድ የሚወዳደረው የለም። ይሁንና የዛሬው መጣጥፌ ዓላማ በወጣቱ ትውልድም ይሁን በሌላ ዕድሜ ክልል ባለው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ላይ ያነጣጠረ አይደለም። በድርጅቶች በተለይም በኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ረገድ በመጪው 2002 ዓ/ም በወያኔ ሙሉ ቁጥጥር ስር ሊካሄድ ስለሚችለው “ምርጫ” ጥቂት ለማለት ፈልጌ ነው ብዕሬን ያነሳሁት።

ካልተሳሳትኩ መጪው “ብሔራዊ ምርጫ” አራተኛው መሆኑ ነው። የአራቱም አዘጋጅ ደግሞ ወያኔ ነው። ለመሆኑ ሕዝብ ዳኛ የሚሆንበትን ምርጫ ወያኔ እንዲያዘጋጀው ማን ሾመው? ሊቋቋም የታሰበው የሕዝብ መንግስት ከሆነስ ወያኔ እንዲያዘጋጀው ማን ሰየመው? ሊቋቋም የታሰበው የሕዝብ መንግስት ከሆነ ደግሞ ለሕዝቡ የሚሆነውን ወያኔ እንዴት ሊያውቅለት ቻለ? ባለፉት ሶስት “ምርጫዎች” የኢትዮጵያ ሕዝብ በነቂስ ተሳትፎ ለእኔ ከፍተኛውን ድምፅ ሰጥቷል ብሎ ወያኔ ራሱ ለዓለም ሁሉ ሲናገር ተደምጧል። ወያኔ ተወዳዳሪ ነው መራጭ? ውጤቱን ማን ነገረው? በሌላ በኩል ደግሞ በምርጫው ማግስት የታሰረ የተንገላታና የተገደለ ኢትዮጵያዊ ቁጥር ብዙ ነበር ማለትን ከሃገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከውጭም ተዘግቦ አድምጠናል። ማን አሰረው? ማን አንገላታው? ማን ገደለው? ወያኔ ነው ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው እንዳይባል ደግሞ በምርጫ አንደኛ ወጥቶ ምን ከፍቶት ወደ እስር እንግልትና ግድያ ተሰማራ? ምንም ይሁን ምን ወያኔ በደም የተጨማለቀ ድምፅ መቀበል እንዴት አልቀፈፈውም? መቼም ሃገርና ሕዝብ ካለ የሃገርና የሕዝብ ጠባቂ ሰራዊት ሊኖር የግድ ነው። ታድያ እስር፣ እንግልትና ሞት ሲፈፀም ፀጥታ ጠባቂው የት ነበር?

እንደምን ለሕዝብ ቆሚያለሁ እያለ የሚምልና የሚገዘት አገዛዝ የገዛ ወገኑን ያለርህራሄ ይጨፈጭፋል?

“ራሱ ጠያቂ፣ ራሱ መላሽ” ካላላችሁኝ በስተቀር ከላይ ላቀረብኳቸው ጥያቄዎች ሁሉ እስከዛሬ በቂና ተግባራዊ ምላሽ መስጠት ያልተቻለበት ዋነኛው ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋሻና መከታ የሚሆነው፣ በቂ አመራር የሚሰጠው፣ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለሚደረገው ሽግግር ቅድሚያ መደላድሉ በሆነው ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ መሟላት ጉዳይ በስልጣን ላይ ያለውን የወያኔ አገዛዝ ማስገደድ የሚችል ጠንካራ የተቃዋሚ ህብረት መፈጠር አለመቻሉ ነው። የተቃዋሚው ሃይል ዛሬም ባንድ መቆም አልቻለም። ባንድ መቆም እንዲቻል ብርቱ ጥረት የተደረገባቸው ድካሞች ሁሉ ጥቂት ራመድና ብዙ ቆም እያሉ እስካሁን ድረስ ቀጥለዋል። የሩቁን ትተን የቅርቡን የቅድመ-ምርጫ 97ቱን ወቅትና ከዚያም በሁዋላ የተከሰተውን የተቃዋሚውን ጎራ ሁኔታ እንኳ መለስ ብለን በጥልቀት ለመመርመር ብንሞክር ለወደፊቱ ምን ማድረግ እንዳለብን የሚያመላክቱ ብዙ ጠቃሚ ልምዶችን መቅሰም እንችላለን።

ያለጥርጥር በኢትዮጵያ ውስጥ በ2002 ዓ/ም ሊካሄድ የታሰበው “ምርጫ” አሁን ከሚታየው ጭብጥ ሁኔታ በመነሳት የሰከነ የፖለቲካ ውድድርን ጋብዞ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግርን ሊያመጣ የሚችልበት ዴሞክራሲያዊ ህይወት የለውም። ወያኔ ከ97ቱ የምርጫ ተመክሮ ተነስቶ፣ የበለጠ እመቃና አፈናውን አጠናክሮ፣ የተቃዋሚዎችን መሪዎች አስሮ፣ ራሱን ለተጨማሪ የስልጣን ዘመን ለማብቃት ደካማ ድርጅቶችንና መሪዎቻቸውን ይዞ ነው “ምርጫ” የሚለውን ትዕይንት ማካሄድ የሚፈልገው። ምርጫ ቢያንስ ገዢው ፓርቲ ለለውጥ የተዘጋጀ ሲሆንና ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ለማድረግ በብሄራዊም ሆነ በዓለም

ይኖራል ለማለት ይቸግራል። ሆኖ መገኘት እንጂ ያቃተው የሆነውን በሰላ ምላስ በማወራረድ ረገድ አዲሱን ትውልድ የሚወዳደረው የለም። ይሁንና የዛሬው መጣጥፌ ዓላማ በወጣቱ ትውልድም ይሁን በሌላ ዕድሜ ክልል ባለው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ላይ ያነጣጠረ አይደለም። በድርጅቶች በተለይም በኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ረገድ በመጪው 2002 ዓ/ም በወያኔ ሙሉ ቁጥጥር ስር ሊካሄድ ስለሚችለው “ምርጫ” ጥቂት ለማለት ፈልጌ ነው ብዕሬን ያነሳሁት።

ካልተሳሳትኩ መጪው “ብሔራዊ ምርጫ” አራተኛው መሆኑ ነው። የአራቱም አዘጋጅ ደግሞ ወያኔ ነው። ለመሆኑ ሕዝብ ዳኛ የሚሆንበትን ምርጫ ወያኔ እንዲያዘጋጀው ማን ሾመው? ሊቋቋም የታሰበው የሕዝብ መንግስት ከሆነስ ወያኔ እንዲያዘጋጀው ማን ሰየመው? ሊቋቋም የታሰበው የሕዝብ መንግስት ከሆነ ደግሞ ለሕዝቡ የሚሆነውን ወያኔ እንዴት ሊያውቅለት ቻለ? ባለፉት ሶስት “ምርጫዎች” የኢትዮጵያ ሕዝብ በነቂስ ተሳትፎ ለእኔ ከፍተኛውን ድምፅ ሰጥቷል ብሎ ወያኔ ራሱ ለዓለም ሁሉ ሲናገር ተደምጧል። ወያኔ ተወዳዳሪ ነው መራጭ? ውጤቱን ማን ነገረው? በሌላ በኩል ደግሞ በምርጫው ማግስት የታሰረ የተንገላታና የተገደለ ኢትዮጵያዊ ቁጥር ብዙ ነበር ማለትን ከሃገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከውጭም ተዘግቦ አድምጠናል። ማን አሰረው? ማን አንገላታው? ማን ገደለው? ወያኔ ነው ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው እንዳይባል ደግሞ በምርጫ አንደኛ ወጥቶ ምን ከፍቶት ወደ እስር እንግልትና ግድያ ተሰማራ? ምንም ይሁን ምን ወያኔ በደም የተጨማለቀ ድምፅ መቀበል እንዴት አልቀፈፈውም? መቼም ሃገርና ሕዝብ ካለ የሃገርና የሕዝብ ጠባቂ ሰራዊት ሊኖር የግድ ነው። ታድያ እስር፣ እንግልትና ሞት ሲፈፀም ፀጥታ ጠባቂው የት ነበር? ከሃገርና ከሕዝብ ሌላ ክቡር ነገር ፓርቲና ባሕል እንዲኖር ግፊት ማድረግ ይጠበቅበታል። የግለ-ሰብ አምልኮና የግለሰብ የበላይነት በድርጅቶች ውስጥ እንዳይፈጠርና ተፈጥሮም ከሆነ በብርቱ መታገል ያስፈልጋል።

- የድርጅት መሪዎችን ተቻኩሎ አንጉል መካብ የማንአለብኝነትና የአልተካም-ባይነት ስሜት በመፍጠር ላይና ወደፊትም የሚፈጥረውን ቀውስ አስቀድሞ በማሰብ በተግባራዊ አስተዋፅኦ ላይ ብቻ የተመረከዘ ተገቢና በቂ እውቅና ብቻ የመስጠት የፖለቲካ እውነታን መፍጠር ይገባል።

- በድርጅቶች ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አሰራርና ስልጣንን በተመለከተም የተወሰነ የጊዜ ገደብ እንዲኖረው ማድረግ በጣም አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን አንዱ የዴሞክራሲያዊነት መገለጫ መሆኑን ማወቅና መተግበር ያስፈልጋል። የድርጅቶች አባላት ብቻ ሳይሆኑ ሕዝብም ለዚህ ተግባራዊነት በየመስኩ ግፊት ማድረግ ይኖርበታል።

- የፖለቲካ ድርጅቶች ለህብረት ትግል ምሥረታ ቀዳሚ ትኩረት እንዲሰጡና ተግባራዊም እንዲያደርጉ ሕዝብ ጫናና ግፊት በማድረጉ መቀጠል አለበት።

- በህብረትጥያቄ ዙሪያ የሚቀርቡ አላስፈላጊ ምክንያቶችን ያለመቀበልና ድጋፍን መንሳት ይገባል።

- በተቃራኒው ደግሞ ለህብረት ስምረት የሚደክሙትን ማበረታትና ቀጣይ ድጋፍም መስጠት ከሕዝብ የሚጠበቁ ጉዳዮች ሲሆኑ የድርጅት አባሎችም በበኩላቸው ድርጅቶቻቸው በዚህ ጥረት ላይ እንዲያተኩሩ ማበረታታት፣ መግፋትና ማስገደድ ይኖርባቸዋል።

በተቃዋሚዎች በኩል እስካሁን በፖለቲካው መድረክ ሕዝባዊ ወገንተኝነታቸውን በምግባራቸው ያረጋገጡቱ የግድ ባንድ ላይ መቆምና መምከር ቀዳሚ ግዴታቸው ነው። በዚሁ ሂደት ወያኔ በተቃዋሚ ስም ያስቀመጣቸውን ለይቶ ማወቅና እነዚህን ያላካተተ ከአስመሳዮች የጠራ ትግል ማድረግ ወቅቱ የሚጠይቀው ዋነኛ ጉዳይ ነው።

የወያኔ ተቀጥላዎች በተቃዋሚ ስም ለወያኔ የስልጣን ማራዘሚያ የተተከሉ መሆናቸውን ማጋለጥም የትግሉ አካል መሆን ይኖርበታል። ለዚህ ዓቢይ ምሳሌ የሚሆነው በአቶ ልደቱ አያሌው የሚመራው ተቃዋሚ ተብዬ ድርጅት ነው። ይህ ድርጅት የወያኔን ዕድሜ ለማራዘም የተተከለ አሻንጉሊት መሆኑን በይፋ ማጋለጥና ከዚህ ስብስብ ጋር ትብብር ላለማድረግ ቁርጠኛ ውሳኔ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ በአቶ ልደቱ የሚመራውን ተቃዋሚ ተብዬ እንደተቃዋሚ ቆጥሮ የሚካሄድ ድርድርም ሆነ ህብረት ከተጀመረ መጨናገፉና ብሎም የጋራ ትግሉ ገና ሳይንቀሳቀስ ከጅምሩ እንደሚሽመደመድ አስቀድሞ መታወቅ ይኖርበታል።

ስለሆነም ሃቀኛ ተቃዋሚዎች ከአስመሳዮች ፀድተው በፍጥነት በጋራ ለመንቀሳቀስ መወሰንና ወያኔን የማስወገዱን ትግል ወደፊት ማራመድ ይጠበቅባቸዋል። ባሁኑ ወቅት ሃገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱቱ ከገዢው ቡድን ጋር በጀመሩት ድርድር ሂደት በፕሮቶኮል፤ በምርጫ አካሄድና ባሕርይ ዙሪያ ላይ ብቻ በማተኮር ሳይሆን የታሰበው ምርጫ ነፃና ፍትሓዊ በሚሆንበት ጉዳይ ላይ ማተኮር ይኖርበታል። ነፃ የምርጫ ቦርድ፣ ነፃ ሚዲያ፤ የሃገር ውስጥና የውጭ ታዛቢዎች የግድ መገኘት፣ የፖለቲካ እስረኞች አለምንም ቅድመ-ሁኔታ መፈታት፣ ነፃ የጥበቃ ክፍል መኖር ቀዳሚ ትኩረት ከሚሹት ጉዳዮች ዋነኞቹ ናቸው። ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳን አስሮ የምትመራውን ድርጅት በነጻና ፍትሓዊ ምርጫ አሳትፋለሁ የሚለው አባባል ቧልት ብቻ ሳይሆን ድፍረትም ነው።

የነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላትን እውን ከማድረግም ባሻገር በቂ የምርጫ ዝግጅት ማድረጊያ ጊዜን ለማግኘት የምርጫውን ወቅት ለማራዘም መጣርም የትግሉ አካል ሊሆን ይገባል። በሃገር ወሰጥ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች አሁን ካሉበት ሁኔታ ወጥተው አበረታችና ተጨባጭ ውጤት ወደሚያስገኙ የትግል አቅጣጫዎች ሊያተኩሩ የግድ ነው። በአምባገነኑ አገዛዝ ህገ-ወጥ ተብለው የተፈረጁትም ወገኖች ትግላቸው የተቃዋሚውና ህዝባዊው ትግል አካል ነውና በሃገር ውስጥ ካለው ትግል ጋር የሚቀናበርበትና የሚቀናጀበት ግንኙነት ተፈጥሮ የጋራ ትግልና ትብብር የሚደረግበት መንገድ ሊፈለግ ይገባል።

በህገ ወጥነት የተፈረጁ ድርጅቶች በመጪው "ምርጫ" ጉዳይ ላይ መግባባትና የጋራም ድምፅ ሊኖራቸው የግድ ነው። በጋራ የሚመካከሩበት ሁኔታን መፍጠሩ ከሌሎች ጋር ለሚኖራቸው ግንኙነት የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ባስቸኳይ ተግባራዊም መሆን ይኖርበታል። በየመስኩ የሚደረገው ትግል በጋራ ሆኖ መቀጣጠል ከቻለ አምባገነኑን ስርዓት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እስከማሳጣት የሚያስችለው ዘዴ ቀላል ሊሆንና ተደማጭነትንም ጭምር ሊያስገኝ ይችላል። ካሁን በሁዋላም ቢያንስ በአራት ግንባሮች መንቀሳቀስ ይቻላል። በተለይ፦

- የፖለቲካ ድርጅቶች ግልፅ የሆነ

ውይይት በማድረግ ከጋራ ስምምነት ላይ መድረስና ይህንንም ለሕዝብ ይፋ ማድረግ፤

- በውጭ ሃገሮች የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ባንድ ቆሞ ለጋራ ትግሉ የበኩሉን አስተዋጽዖ የሚያበረክትበትን መድረክ መፍጠርና በቶሎ ማንቀሣቀስ፤

- የውጭ መንግስታትን ሳያሰልሱ መወትወትና የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን ዕጣ ፈንታ በመወሰን ረገድ ከማናቸውም ዓይነት ጫናዎች ነጻ ሆኖ እንዲወስን ሊረዳ የሚችልበትን መንገድ ማሳየት፤ ለዚሁም እንዲያግዝ ስብሰባዎች፣ ሲምፖዚየሞችና ሌሎች የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት፤

- ማናቸውም በውጭ ሃገሮች የሚደረጉ የተቃውሞ ትግሉ አካል የሆኑ በድርጅት ደረጃም ሆነ በሙያ መስክ እንዲሁም በቡድንና በግል የሚደረጉ የዜግነት ግዴታ እንቅስቃሴዎች በሃገር ውስጥ ከሚደረጉ ጥረቶች ጋር ትስስርና ትግግዝ እንዲኖራቸው ማስቻል አስፈላጊና ዋነኞቹ ናቸው።

የፖለቲካ ድርጅቶች ባሁኑ ሁኔታ ከላይ የተጠቀሱትን እንኳ ማድረግ ከቻሉ ወደፊት ሊፈጠር ለሚታቀድ ሰፊ ሕብረት ታላቅ መሰረት እንደጣሉ ይቆጠራል። በመጪው 2002 ዓ/ም ምርጫ አሁን ባለው ሁኔታ "ተወዳድሮ ለማሸነፍ የሚደረግ ሩጫ ለወያኔ መንግስት ሕጋዊ ሽፋን ከመስጠቱም ባሻገር ተቃዋሚውን ከፋፍሎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታ ሳይሆን እንዲቀር የሚያደርግና ሽንፈትንም አላብሶ በሕዝባዊው ትግል ላይ የማይሽር ጠባሳ ትቶ የሚያልፍ ድርጊት ይሆናል።

የተቃዋሚ ወገኖች ከታሪክ ተወቃሽነትም ሆነ ከህሊና ጠባሳ ነፃ የሚሆኑበትን ሃገራዊ አደራቸውን ሊወጡ ይጠበቃል። ያለንበት ወቅት በዚህና በዚያ ምክንያት እየተባለ የምንለያይበት ወቅት አይደለም። "ህጋዊ ነኝ፤ ህጋዊ ያደረገኝ አካል ደምወዜንና ሌሎችንም ይነሳኛል" እየተባለ ለወያኔ ሕግ ተገዢነትን የምናፀድቅበት ወይም በሱ ፈቃድና ፍላጎት የምንቀሳቀስ ከሆነ ትግሉ ዓላማውን እንዳይስት ያሰጋል። በወያኔ ሕግና ፈቃድ ብቻ ታጥሮ የሚንቀሳቀስ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት መሪ ቢኖር ለአመራር ብቁ ሊባል አይገባም። ለምን ቢሉ እንዲህ ዓይነቱ መሪ ራሱን ገና ነፃ ስላላወጣ ሌላውን ነፃ በማውጣት ትግል ውስጥ ተሣትፎ የሚጠበቅበትን ሃላፊነትና ግዴታ በበቂ ሊወጣ አይቻለውምና!

ቁርጠኝነትና መስዋዕትነት ከቀራጥ የሕዝብ መሪዎች ምንጊዜም ይጠበቃል። ወያኔ ስልጣኑ ሕጋዊነት የለውምና "ሕጋዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር አልገናኝም፤ አብሬ አልሰራም፤ ወያኔ አይፈቅድልኝም...ወዘተ" የሚሉ ሰበብ አስባቦች ሚዛን አይደፉም፤ ጨርሶ ትክክለኛም አይደሉም። ይልቁንም ሕዝብን ከአምባገነን ለማላቀቅ የሚደረገው ትግል የሚጠይቀውን ማናቸውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ቁርጠኛ ሆኖ በሚስጢርም ሆነ በተለያዩ ዘዴዎች ከሕዝብ ወገን ተቃዋሚዎች ጋር በማበር የኢትዮጵያን ሕዝብ የትንሳዔ ቀን ለማቃረብ ተግቶ መስራቱ ትኩረት ሊሰጠው የግድ ነው።

የጋራ ትግል በሚደረግበት መንገድ ላይ ተስማምቶ በጋራ ከሚደረስበት ውሳኔ በመነሳት በጋራ መንቀሳቀስ እንጂ የወያኔን ህግ ሰበብ እያደረጉ "ከናንተ ጋር በህብረት ለመስራት ችግር አለብኝና እርዳታችሁን ብቻ ላኩልኝ" የሚል የተቃውሞ ትግል ሃቀኝነት ይጎድለዋል። ይህ ዓይነቱ አካሄድ ሊበረታታም፤ ሊደገፍም አይገባም።

ስለሆነም መጪውን የ2002 ዓ/ም ምርጫ

ለሕዝባዊው ትግልና ለሕብረት ቀጣይነት ልንጠቀምበት ይገባል። ትግሉም የኢትዮጵያን ሕዝብ እያሳተፈና እያሳወቀ መቀጠል አለበት። የኢትዮጵያን ሕዝብ ያላሳተፈ ትግል፣ ሕብረት ወይም ምርጫ ከንቱና ፍሬ ቢስ ነው። ይልቁንስ የወቅቱ መፈክራችን "መጪው ምርጫ ለትግልና ለሕብረት" ይሁን!!!

....//....

## በሕዝብ ሚዲያ ምትክ የፓርቲ ሚዲያ (የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፀጋ)

**(ቱሉ፤ ከዋሽንግተን ዲሲ)**

አያልቅበት ነውና ህወሓት/ኢ.ሕአዴግ፤ "አንድ መንግስት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ቆርጠ ከተነሳ የመንግስት ሚዲያም ትልቅ የዴሞክራሲ መሳሪያ ይሆናል" ይለናል- በገቢር ሳይሆን በተገብሮ- ፈረንጆቹ በንድፈ-ሃሳብ ደረጃ እንደሚሉት መሆኑ ነው። እኛ ደግሞ ባለፉት አስራ ስምንት ዓመታት በተግባር ዴሞክራሲ አላየንምና የመንግስት ሚዲያ የዴሞክራሲያ መሳሪያ ሊሆን አልቻለም ባይ ነን።

ይልቁንም የመንግስት ሚዲያ ጋዜጠኞች ሳይወዱ በግድ የገገሮው ቡድን ጋዜጠኞችና ቃል አቀባዮች ሆነዋል እያልን ሙግት ገጥመናል። ለዚህ አባባላችን ማስረጃ መጠየቃችን ስለማይቀር ቅደመ እና ድህረ ምርጫ 97 የሕዝብ መገናኛ ብዙሃንን ሚና ለአብነት አቅርበን ፍርዱን ለእናንተ እንተዋለን። 1997 ዓ/ም በመንግስት ሚዲያ ለሚሰሩ ጋዜጠኞች የፈተና ወቅት ነበር። ለዴሞክራሲ በሚሰራ ጣቢያ ውስጥ መስራት ይቻላል በሚል ግምት ጋዜጠኞችና ሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ሰራተኞች "ሚዛናዊ" ለመሆን የተነቃቁበት ወቅት ነበር።

ለጋዜጠኞቹ ፈተናው ቀላል አልነበረም። የምርጫ 97ን ሂደት ለመዘገብ ወደተለያዩ ያገሪቱ ክፍሎች የተንቀሳቀሱ ብዙ የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥንና ሌሎች በህትመት ዘርፍ የተሠማሩ የመገናኛ ብዙሃን ሰራተኞች ወደየጣቢያዎቻቸው ሲመለሱ ያስደነገጠ ክስተት አፍጥጦ ጠበቃቸው። ከፊሎቹ "ኮንትራታችሁ አይታደስም" ተባሉ። በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት አባልነት ተጠረጠሩ። የመንግስት ደጋፊ የሆኑና ያልሆኑ የሚል ቀጥያ የተሰጣቸው ጋዜጠኞች ከመቅጽበት ተፈጠሩ። ለነገሩ ፈተናው ወደየጣቢያቸው ሲመለሱ ብቻ ሳይሆን የምርጫውን ሂደትና ውጤት ሊዘግቡም በሄዱባቸው ቦታዎች "ኢቲቪ" እየተባሉ ጣት ይቀሰርባቸው ነበር። ከሁለት ያጣ ቢላዋ ይሏል ይኸው ነው።

ይህ ዐይነቱ ችግር የደረሰበት አንድ ጋዜጠኛ "የሚያበሳጭ ግን የማይረሳ ጊዜ" ይለዋል ወቅቱን። ይኸው ጋዜጠኛ በሰኔ 1997 ዓ/ም ያስተናገደውን አንድ አጋጣሚ ከቶም አይዘነጋውም። በህወሓት/ ኢ.ሕአዴግ የተሾመ አለቃው እንዳዘዘው የተመደበበትን ዕለት ክንውን ሊዘግብ ወጣ። ወቅቱ ውጥረት የተሞላበትና ፖለቲካ የተሟሟቀበት ጊዜ ነበር። በተቃዋሚዎች፣ በኢ.ሕአዴግና ተሣትፎ ባደረገው የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ መካከል የሚደረገውን ውይይት ለመዘገብ ይህ ጋዜጠኛ በቦታው ተገኘ። ያየውን ሁሉ በድምፅና በምስል ቀርጸ ጮማ ዜናውን እያሰበ ወደ ስቱዲዮ ገሰገሰ። ከስቱዲዮው ሲደርስ ግን እውነታው ሌላ ሆነ። እርሱ በዋለበት ውይይት ያልዋለ ሰው ዜናውን ቀድሞ ከትቦ ጠበቀው። የዜናው ፀሐፊ ተብዬ ስለውይይቱ የሚያውቀው አንዳችም ጉዳይ አልነበረም። ነገር ግን የውይይቱ

ሂደትና ውጤት፣ ምን ሆነ ምን፣ ዜናው እንዲሠራ የተፈለገው መንግሥት ተብዬው በሚፈልገው መልኩ መሆኑ ተነገረው፣ ምሽት ላይም ዜና ተብዬው ተላለፈ። ባድናቆትና በግርምት የራሱን ዜና ሰማ። ለራሱ "እዚህም ተደረሰ?" አለ። እዚህ ተደርሷል - በአብዮታዊ ዴሞክራሲ።

ይህም ብቻ አይደለም ከምርጫ 97 በሁዋላ ሚዲያ ወደ አንድ ፓርቲ መገልገያነት ተቀየረ። ከምርጫ 97 በፊት በመንግስት ባለቤትነት የተያዙት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች 54 ከመቶ የሚሆነውን የአየር ስርጭት ሰዓታቸውን ለተቃዋሚዎችና ለሌሎች ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ሊሰጡ ቃል ገብተው ነበር። ቃል ግን ተግባር ሳይሆን ቀረ - የሚያዝበት ህወሓት/ኢሕአዴግ ነውና። ከምርጫ 97 በሁዋላ የሕዝብ መሆን የሚገባው ሚዲያ ያንድ ፓርቲ ሲሆን የሚሰማው ድምፅ ሁሉ የአንድ ወገን ብቻ እንደሆነ ዛሬም ድረስ ቀጥሏል። የሚገርመው የተገባው ቃል ለምን ተቀለበሰ? ብለው ሊጠይቁ የሚገባቸውና ማድረግም ያለባቸው የመገናኛ ብዙሃን ክፍል ሰራተኞች የሚሰሩባቸውን ጣቢያዎች እንዲለቁና የተቀሩትም በዝምታ የታቀቡ ጋዜጠኞች እንዲሆኑ ተገደዱ። መኖር ያለባቸውም የተባሉትን የሚያስፈፅሙ ሆኑ። አዲዮስ ሊብራል ዴሞክራሲ! እንኳን ደህና ገባህ አብዮታዊ ዴሞክራሲ! ማለት እንጂ ምን ይባላል?

ዕውን ዴሞክራሲ ቢኖር ኖሮ በመገናኛ ብዙሃን ኤዲቶሪያል ክፍል ውስጥ ሕዝብን ማገልገል፣ ሐቀኝነት፣ ሚዛናዊነት፣ ተጠያቂነት የፖሊሲዎች ዋነኛ ማጠንጠኛዎች በሆኑ ነበር። የህወሓት/ ኢሕአዴግ ተሿሚዎች ለዴሞክራሲ ቀመናል ይበሉ እንጂ እንዲህ ዓይነቶቹ ፖሊሲዎች አይነበቡላቸውም። በአኳያው የመንግስት ተብለው የሚጠሩት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ከኢትዮጵያ ሕዝብ በሚሰበሰብ ታክስ የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ሕዝብ እያስተዳደራቸው ግን የሕዝብ አይደሉም።

በ1980ዎቹ በሕዝባዊው ትግል ሊወለዱ የቻሉ የግል መገናኛ-ብዙሃን ብቅ ከማለታቸው እንግዳ ድምፅ ነው የተስተጋባባቸው። ህወሓት/ኢሕአዴግ እንደሚደሰኩረው ሳይሆን የግል መገናኛ-ብዙሃንን የወለደው የስርዓቱ ቸርነት ሳይሆን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ምስረታ ጥያቄዎች ማየልና መዳበር ነው። በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ በእርግጥም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የለውጥ ግፊት ተበራክቶ ነበር።

አንዳንድ የዋሆች ህወሓት/ኢሕአዴግ ወደ ስልጣን ሲወጣ ነው የግል ሚዲያዎች የተከፈቱ ሊሉን ይሞክራሉ። ስርዓቱን እንዲህ አሞግሰው ሳይጨርሱ ደግሞ በራሱ በስርዓቱ ተቀርጥፈው የተበሉ የግል ሚዲያ ዘርፎችን ቆጥረው መጨረስ ይታክታቸዋል። ለውጥ መጣ ማለትን ይደፍሩና ለውጥ ሄደ ማለትን እንደ ወላፈን ይፈሩታል።

የሕዝብ ወገኖችና ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች አጥብቀው በመከራከርና በመጠየቅ ላይ ያሉት "የግል ሚዲያ በወረቀት የመፈቀዱን ያህል ማገቻውም አብሮ ተፈጥሯል፣ ነፃ ሚዲያ ዛሬም የለም፣ እንዴትና ለምን ሆነ?" እያሉ ነው። የሆነው ነገር ሁሉ "በቅሎን ከነገመዷ" እንዲሉ ነው። የሕዝብ የለውጥ ፍላጎት የከፈተውን ሚዲያ ህወሓት/ኢሕአዴግ ባዛኙ ናዛዥነት ወዲያው ከረቸመው። የግሉን ሚዲያ ጋዜጠኞች እንደመንግስት ሚዲያ ጋዜጠኞች ሁሉ የአንድ ፓርቲ ጋዜጠኞች

ካልሆናችሁ በሚል ማመስ ጀመረ። በዚሁ ሳቢያም የግል ሚዲያ ከህወሓት/ ኢሕአዴግ ጋር ሆድና ጀርባ መሆን ብቻ ሳይሆን ያይጥና ድመት ያህል ማሳደድና መሳደድ ተከተለ። የግሉ ሚዲያ ዘርፍ ሠራተኞችም በጻፉትም ባልጻፉትም ለክስና ለእስራት ተዳረጉ። ብዙዎቹ ተዘጉ። በመጨረሻም ለስርዓቱ የሚስማማ የነፃ ፕሬስ ህግ ባዋጅ ተደመጠ።

አዲሱ ዴሞክራሲና ፍፁማዊ የበላይነት ትርጉማቸው አንድ ሆነ። በደርግስ ጊዜ ሚዲያው በሰራተኞቹ ፓርቲ ኢሠፓ ፍፁማዊ ቁጥጥር ስር አልነበረምን? ልዩነቱ ምኑ ላይ ነው? "ስልቻ ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ ስልቻ" ።

ስለምርጫ በተለይም ስለመጪው 2002 ዓ/ም "ምርጫ" ብዙ በሚወሳበት ባሁኑ ወቅት የነፃ ሚዲያ መኖር ወሳኝ ነው። የግሉ ሚዲያ በህወሓት/ኢሕአዴግ ክንድ ይበልጥ እየደቀቀ ባለበትና የሕዝብ መሆን የሚገባው ሚዲያ በስርዓቱ ፍፁም የበላይነት ቁጥጥር ስር በሆነበት ባሁኑ ወቅት ምርጫው ነፃና ፍትሓዊ መሆኑ እንዴት፣ በምን መንገድና በማንስ ይዘገባል? ህወሓት/ኢሕአዴግ እንደትናንቱ ሁሉ ዛሬም የምርጫው ካርድ ተቆጥሮ ሳያልቅ አሸናፊነቱን የሚያውጅበትና ፍፁማዊ የበላይነቱን ያረጋገጠበት የመንግስት ሚዲያን ከነሰራተኞቹ አፍኖ ይዟል።

የምርጫ ኮሮጆ እየገለበጠም ቢሆን ነገም በይፋ አሸናፊ ነኝ የሚልበትን መገናኛ ብዙሃንን ተቆጣጥሯል፣ ደፈር ብለው ትንፍሽ እንኳ ለማለት የሚሞክሩ ቢኖሩ በቶሎ ሊያፍናቸው የሚችልበት ሃይል አለውና እንደልማዱ እያሳደደ ከማጥፋት አይመለስም።

ለሃገራቸውና ለህዝባቸው የህይወት መስዋዕትነት ጭምር ለመክፈል ቆርጠው ሊነሱ የሚችሉ የሚዲያ ዘርፍ ሠራተኞች ነፃነታቸው ሳይረጋገጥ መጪው ምርጫ ነፃና ፍትሓዊ ይሆናል ብሎ ማሰብ ቅዠት ይሆናል ቢባል ከስድብ ይቆጠር ይሆን?

መቼም ዕብደት ካልሆነ በስተቀር በውጭ ሚዲያ መጠቀም ይቻላል ብሎ መደምደም አይቃጣም። እነቪ.ኦ.ኤ፣ የጀርመን ድምፅ ራዲዮ፣ ወዘተ፣ አሉልን እየተባለም ሊፎከር ይቃጣ ይሆናል። አዎን እስካሁን በነዚህ የዜና ምንጮችና በሌሎችም በሚገባ ተጠቅመናል። እርግጥ ነውና ልንክድ አይቃጣንም። ውለታቸውንም ጨርሶ አንዘነጋም። በነፃ ምድር የተቋቋሙና ከነፃ ምድር የሚተላለፉ ስለሆኑ ነፃነታቸው እያስጎመጀንም ቢሆን በነፃነት ነፃነት ስለማጣታችን መስክረውልናል። እሰየው ሃቀኛ አይጥፉ። ግና የራሳችን ነፃ ሚዲያ ኖሮን ስለራሳችን የነፃነት ትግል የምንዘገበው መቼ ነው? የሕዝባዊው ትግል አንዱ ዓላማስ ይኸው አልነበረምን?

ለነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ነፃ ሚዲያ ዋነኛ ቅድመ-ሁኔታ ብቻ ሳይሆን መሰረታዊ ጉዳይም ነው። በሃቀኛና ተጨባጭ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ መረጃን በማቅረብ በሕዝብ ዘንድ ተአማኒነትን ያተረፈ፣ ከማንም ተፅእኖ ነፃ የሆነ ሚዲያ መኖር ለህብረተሰብ ዕድገት ወሳኝ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው። መቼም ጉድ ሳይሰማ አይታደርምና ሰሞኑን ደግሞ ህወሓት/ ኢሕአዴግ ድርድሩም በድብቅ መሆን አለበት እያለን ነው። መደባበቅን ምን አመጣው? በድብቅና በጓዳ በሚፈፀሙ ድርጊቶች ሃገርና ሕዝብ በአደባባይ እየደማ መደባበቅና በጓዳ መደራደርን በጭራሽ መፍቀድ የለብንም። ቢያንስ ብርቄ ሬዲዮኑን ተንተርሶ ለሚጠብቀን ወገን ሁሌም ሃቁን! ሁሌም ገሃዱን። ነፃ ሚዲያ!!!

# ዜናዎች ከዚህም ከዚያም

## በምዕራብ ካናዳ የኢሕአፓ (ዴ) አባላት ስብሰባ ተካሄደ

በምዕራብ ካናዳ የሚገኙ የኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አባላት ከነሐሴ ፴ እስከ ጳጉሜ ፩ ፪ ሺህ ፪ ዓመተ-ምህረት ለሁለት ተከታታይ ቀናት ያደረጉትን ዓመታዊ የሪጅን ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቃቸውን በቦታው ተገኝቶ የነበረው የዜና ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ዘጋቢ ገለጠ። ዘጋቢያችን አያያይዞ እንደገለጸው የሪጅኑ አባላት በተለይም ድርጅቱ ከለውጥ አጋቹ ክፍል ከተለየ በሁዋላ ተመሳሳይ ሪጅናዊ ስብሰባ ሲያደርጉ ይህ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑን ጠቅሶ በተደረገውም ስብሰባ ላይ ባካባቢው ከሚኖሩ አባላት ከዘጠና በመቶ በላይ መገኘታቸውንም ጠቁሟል። የስብሰባው ተካፋዮች በሁለቱ ቀናት የስብሰባ ወቅት ልዩ ልዩ ድርጅት ነክ ጉዳዮች ላይ በጥልቀት መወያየታቸው ሲታወቅ ከግንቦት ፩ ፪ ሺህ ፩ እስከ መስከረም ፩ ፪ ሺህ ፪ ዓ.ም. ድረስ ባካባቢው ለተከናወኑና ላጋጠሙ ችግሮችም ትኩረት በመስጠት ሰፊ ውይይት መደረጉን ለማወቅ ተችሏል።

በዚሁም ስበሰባ ወቅት የምዕራብ ካናዳ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ በጥልቀት ከመገምገሙም ባሻገር ስለ ሪጅኑ አባላት ተሳትፎ ይበልጥ መጠናከር፣ ስለሪጅኑ መዋቅር መስፋት፣ በሪጅኑ ከሚንቀሳቀሱ ሌሎች ድርጅቶች ጋር ሕዝባዊውን ትግል አቀናጅቶ እንዴት ማጎልበት እንደሚቻልና ድርጅቱን በፋይናንስ በኩል ለመርዳት በስፋት መከናወን ስላለባቸው ጉዳዮች የሰከኑ የሃሳብ ልውውጦች መደረጋቸው ስብሰባውን ስኬታማ ሊያደርገው እንደቻለም ተያይዞ ተገልጿል። ከዚህም በተጨማሪ በስብሰባው የተገኙት የሪጅን አባላት በሪጅኑ ባለፉት አስራ ሶስት ወራት ውስጥ በሂደት ስለተገኙ ውጤቶች ብቻ ሳይሆን በእቅድ ተይዘው፣ ነገር ግን በልዩ ልዩ ምክንያቶች ተግባራዊ ሳይሆኑ በቀሩ ጉዳዮችም ዙሪያ በግልፅነት በመወያየት ባስቸኳይ ወደ ተግባር እንዲቀየሩ የሚያስችሉ መፍትሂዎችንም ማመንጨታቸው ታውቋል።

በመጨረሻም መደረግ ስላለባቸው ያካባቢ ያጭርና የረጅም ጊዜ የወደፊት ዕቅዶች ገንቢ ሃሳቦችን በመለዋወጥ ውሳኔዎች አሳልፈውና ድርጅታቸውንም ለማገዝ ይረዳ ዘንድ ልዩ የገንዘብ መዋጮ በማድረግ ስብሰባው በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁ ተገልጿል።

**(የዜና ኢሕአፓ (ዴ) ዘጋቢ፣ ሬጃይና፣ ካናዳ)**

## የአውሮፓ ህብረት በመጪው ምርጫ ላይጋበዝ?

በ2002 ዓ/ም በኢትዮጵያ በሚካሄደው ምርጫ የካርተር ማዕከል በታዛቢነት መጋበዙን የማዕከሉ ዳይሬክተር ዴቪድ ኤስ ኤቲ ከህወሓት/ኢሕአዴግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሃላፊዎች ጋር መነጋገራቸውን ጭምር በመጥቀስ ከአዲስ አበባ የተላለፈልን ዜና አረጋግጧል። በዚህም ዜና መሠረት ሚስተር ዴቪድ በመግለጫቸው በ97 ምርጫም ማዕከላቸው ሰፊ ተሳትፎ ማድረጉን ጠቅሰው ተመሳሳይ ግብዣ ለሌሎችም ይቀርባል የሚል ዕምነት እንዳላቸው መግለጻቸውን ለመረዳት ችለናል።

በሌላ በኩል ደግሞ እነዚሁ ምንጮቻችን እንደዘገቡት እስካሁን ለአውሮፓ ህብረት ከህወሓት/ኢ.ሕአዴግ ምርጫ ቦርድ የተላከ ግብዣ አለመኖሩ አነጋጋሪ እየሆነ መምጣቱን በተለይም በዋና ዋና ከተሞች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ መጪውም ምርጫ እንደ 97ቱ ሊሆን እንደሚችል ከፍተኛ ግምትና ስጋት እያሳደረ መምጣቱም ተገልጿል።

የአውሮፓ ህብረት ለረጅም ዓመታት በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብና ቁሳቁስ ለኢትዮጵያውያን በሚል እርዳታ ሲለግስ ቢኖርም በ97ቱ ምርጫ ወቅት በታዛቢነት ተገኝቶ በወቅቱ ተቃዋ ሚዎች ያሸነፉበት የምርጫ ውጤት በስርዓቱ መቀልበሱን በመረጃ አስደግፎ ይፋ በማውጣቱና በማጋለጡ ከገዢው ክፍል በኩል ቂም ሳይቋጠርበት እንዳልቀረ የፖለቲካ ተንታኞች እንደሚገምቱ በመግለጽ ዜና አቀባያችን ዘገባውን ደምድሟል።

**(የዜና ኢ.ሕአፓ ዘጋቢ- ከአዲሰ አበባ)**

## መድረክ ሊደሰሙላ አልደራደርም አለ።

ከሃገራችን ርዕሰ-ከተማ ከአዲስ አበባ የሚደርሱን ዜናዎች እንደሚጠቁሙት ገዢው ቡድን ህወሓት/ኢ.ሕአዴግ በተቃዋሚ ድርጅቶች በተለይም በአንድነትና ስምንት ድርጅቶችን ባቀፈው በመድረክ ላይ የሚያደርሰው ጫና እየበረከተ መምጣቱን ሲገልፁ፤ መድረክም በቅርቡ ይፋ ባደረገው መግለጫው ላይ "ድርድር ለነፃ፤ ፍትሐዊና ተአማኒ ምርጫ እንጂ፤ ለሕዝብ ግንኙነት ጠቀሜታ ወይም ለይስሙላ መሆን የለበትም" ሲል እየተሞከረ ባለው ድርድር ላይ ያለውን አቋም ይፋ አድርጓል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞው የደረሱን ዘገባዎች እንደገለጡት መድረክ ወደ ቅንጅት ደረጃ ለመሸጋገር የሚያስችለውን ቅድመ ዝግጅት አጠናቅቆ መስከረም 30፤ 2002 ዓ/ም በተደረገ ጉባዔ ይህንኑ በተግባር እንዳዋለና መተዳደሪያ ድንቡንም እንዳጸደቀ ለመረዳት ችለናል።

ከውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ለመረዳትም እንደተቻለው መድረክ ቀደም አድርጎ ነሐሴ 22፤ 2001 ዓ/ም ድርድርን አስመልክቶ በፃፈው ደብዳቤ ከህወሓት/ኢ.ሕአዴግ ጋር መደራደር የሚሻው በፖለቲካ ፓርቲዎች ስነ-ምግባር ደንብና ከዚህ ተጓዳኝ በሆኑ ያፈጻጸም ጉዳዮች ላይ ሳይሆን መጪውን ምርጫ ነፃ፤ ፍትሓዊና ተአማኒ ለማድረግ በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ስለመሆኑ፤ የዚህም ጅማሬ አዎንታዊና ለጊዜውም ቢሆን ተስፋ ሰጪና የህዝብንም ድጋፍ ሊያበራክት የሚችል አቋም እንደሆነ ለመረዳት ችለናል። በተለይም የሕግ የበላይነት፣ የምርጫ ቦርዱ ገለልተኝነት፣ ዓለም አቀፍና ብሔራዊ የምርጫ ታዛቢዎች ተሳትፎ፣ ለተቃዋሚ ድርጅቶች መደረግ ስላለባቸው ሙሉ ድጋፎች፣ የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም፣ ስለ የፖለቲካ እስረኞች መፈታትና ለመሰል ጉዳዮች መድረክ ትኩረት መስጠቱም በጎ ጎኖች መሆናቸውን ምንጮቻችን አክለው ገልጠዋል።

ህወሓት/ኢ.ሕአዴግ ያስቀመጠውንና አጀንዳዬን ያስፈጽሙልኛል በሚል ዕምነት እሱ የመረጣቸውን ድርጅቶች ያካተተ ካልሆነ ድርድር አይታሰብም የሚለውን ቅድመ-ሁኔታውን በተመለከተ መድረክ በጭራሽ የማይቀበለው መሆኑን ከመግለፁም በላይ አገዛዙ ላሳየው የአሻፈረኝነት ባሕርይ ሳይሸነፍ ድርድሩን ለጊዜው ማቋረጡም የቁርጠኝነት ፍንጭ መሆኑን ምንጮቻችን አክለው አብራርተዋል።

መድረክ ከዚሁ ጋር በማከል ለድርድር ያቀረበው ሌላው ጉዳይ መብቶቹን እየረገጡ በአባሎቹና ደጋፊዎቹ ላይ ጥቃት ስለሚያደርሱት የገዢው ፓርቲ ካድሬዎችና የአገዛዙ ባለስልጣናት ስለሚያዟቸው የስርዓቱ የፀጥታ ሃይሎች ስለመሆናቸውና ጉዳዩም በቀጥታ የሚመለከተው ህወሓት/ኢሕአዴግን ብቻ ስለሆነ ከሌሎች ጋር በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ድርድርና ውይይት ማድረግ አያስፈልገንም ስለሚለው የመድረክ አቋም በስፋት ተዘግቧል።

በህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች በኩል ደግሞ "ኢዴፓና 'ቅንጅት' ከናንተ ጋር እንደራደርም እያሉ ነው" በሚል በድርጅቶቹ መካከል መቃቃርና የፀብ ጫሪነት መሰሪ ተግባርም እየፈፀሙ መሆኑን መድረክ አስታውቆ ከዚሁ ተልካሻ ድርጊቱ ተቆጥቦ ይልቁንም ወሳኝ የሆኑ የምርጫ ቅድመ-ሁኔታ ላይ ማትኮርና በቀረው ጥቂት ጊዜ ባግባቡ ለቀረቡ ሕዝባዊና ሃገራዊ ጥያቄዎች ገዢው ቡድን በቂ መልስ እንዲሰጥ መድረክ ግፊት እያደረገ ስለመሆኑና ከህወሃት/ኢሕአዴግም ጋር እንደገና የተጀመረው ውይይት ለጊዜውም ቢሆን መቋረጡን መረዳት ችለናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለም ከመድረክ ዋና ጽ/ቤት የወጣው መግለጫ እንደሚያስረዳው "መድረክ ወደ ምርጫው የሚገባው እንደ ሚያዝያ 2000 ዓ/ም ምርጫ የኢሕአዴግን የ"99%" ድል ለማጅብ አይደለም። በነፃ ፍትሓዊና ተዓማኒ ምርጫ ውጤት አምጥቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ የስልጣን መሰረትና ባለቤት ለማድረግ እንጂ" ሲል አቋሙን በግልፅ አሳውቋል።

በቅርቡ የደረሱን ዜናዎች እንዳረጋገጡት መድረክ ወደ ቅንጅት ደረጃ መሸጋገሩንና ዶ/ር መራራ ጉዲናን በሊቀመንበርነት መምረጡን ለማወቅ ተችሏል።

# ከዴሞክራሲያ ማህደር

የይስሙላ ምርጫ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ አይደለም። አጼ ኃይለ ሥላሴ ምርጫ፣ ደርግ ምርጫ፣ ህወሓት/ኢህአዴግ ምርጫ - አንድም ሶስትም ምርጫዎች። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ አገዛዝም ይሁን የደርግ ወይም የህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዞች ሁሉም ምርጫ አከናወንን ቢሉም አንዳቸውም ቢሆኑ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለስልጣን ማብቃት አልቻሉም፤ ሁሉም የስልጣን ዘመናቸውን ለማስቀጠል ተጠቀሙበት እንጂ።

በተለይ ህወሓት/ኢሕአዴግ አዲስ አበባ ለመግባት ጥቂት ኪሎ ሜትር ሲቀረው የመድበለ ፓርቲ ስርዓትን እቀበላለሁ ሲል ይውገርገር እንጂ ከሎንዶኑ የ1983 ዓ. ም. ኮንፈረንስ ጀምሮ ህዝባዊና ሃገራዊ ራዕይ አላቸው ብሎ የሚያምናቸውን ህብረ-ብሔር የፖለቲካ ድርጅቶች በማግለል በራሱ እምነት ዙሪያ ሊሰባሰቡ የሚችሉትን ብቻ በመያዝ ነበር ያለፈውን የአስራ ስምንት ዓመት አምባገነናዊ ጉዞውን የጀመረው። ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም ጋር ተያይዞ ሕዝብ የስልጣን ምንጭ እንዲሆንና ምርጫም እንዲካሄድ በምዕራባውያን ለጋሽ አገሮች በሚደረገው ዓለማቀፋዊ ግፊት ምክንያት ህወሓት/ኢሕአዴግም ምርጫ ተብዬውን በየጊዜው ማካሄድ ቢገደድም፣ እስካሁንም በአስተሳሰብ የሚለዩትንና ሕዝባዊና ሃገራዊ የፖለቲካ አማራጭ ይዘው የሚቀርቡትን ድርጅቶች ከማግለልና ከማጥቃት በሽታው ድኖ የዴሞክራሲ አባወራ ሊሆን አልበቃም። ይልቁንም ዛሬም እንደትናንቱ በነፍጥ የሚያምንና በጠመንጃ የሚገዛ፣ ዛሬም የመድበለ ፓርቲ ጸርና አሜከላ ሆኖ ቀጥሏል።

**(ዴሞ፣ ቅጽ 35 ልዩ ዕትም ገጽ1፣ 2002 ዓ/ም)**

የሶስት ሺህ ዘመን ታሪክ የሚወራላት፤ ተፈጥሮአዊ ተስህቦ ያላትና ጥንታዊ የታሪክ ቅርስ ባለሃብት የሆነች ኢትዮጵያችን ናት። ወራሪና ቅኝ ገዢ ባዕዳንን ተከላክላ፤ ነፃነቷን ጠብቃ፤ ለሁሉም ጥቁር ሕዝብ የነፃነት ተምሳሌት የሆነች የምሥራቅ አፍሪቃዊቷ ሀገር ኢትዮጵያችን ነች።ሁለቱንም ታላቅ ሃይማኖቶች በቀዳሚነት ተቀብላ እስላሙም ክርስቲያኑም ህብረተሰብ ተፈቃቅዶና ተቻችሎ የኖረባት ሀገር ኢትዮጵያችን ነች።

ለሃገሩ ሉዓላዊነትና ለአንድነቱ ግንባሩን ለጥይት፤ እግሩን ለጠጠርና ለእሾህ የሰጠ ጀግና አፍርታ በደምና በአጥንት ድንበሯን ያስከበረች ብቸኛ የጥቁሮች ሃገር ኢትዮጵያችን ነች።

የተለያዩ ጎሣዎችን አካታ፤ በተለያዩ ባህሎች አሸብርቃ፤ የራሷ የተለያዩ በዓላት ያሏት ሀገር ኢትዮጵያችን ናት። ቅድመ የሰው ልጅ መገኛ በመሆኗ፤ ዓለም በቅድመ-ሰው ልጅ አኗኗርና ስልጣኔ ምርምሩ ትኩረቱን የጣለባት ሀገር፤ የአፋሯ ድንቅነሽ ያስመሰከረችላት ኢትዮጵያችን ናት። ገና ባግባቡ ተጠንተው ያላበቁ ጥንታዊ የታሪክ ቅርሶቿ፤ የአክሱም ስልጣኔ፤ የላሊበላ ቤተክርስቲያኖች፤ የጎንደሩ ፋሲለደስ ግቢ፤ የሐረሩ ግንብ፤ የኦሮሞው ገዳ ስርዓትና በርካታ ሌሎች ምሳሌዎች፤ ያቆዩልን መረጃዎችና ገና ምስጢረ-ኢትዮጵያዊነታቸው እየተጠኑ ያሉባት አፍሪካዊት ሀገር ኢትዮጵያችን ናት።

የራሷ ፊደል ባለቤት ሆና የሕዝቧን ጥንታዊ ገድሎች በቋንቋዎቿ ለታሪክ ያኖረች ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት። እርግጥም ኢትዮጵያዊነት የታሪክ ባለቤትነት ነው፤ ኢትዮጵያዊነት ኩራት ነው።

**(ዴሞ፤ ቅጽ 34 ቁጥር 2 ገጽ 1 2001 ዓ/ም)**

# የሴቶች ዓምድ

## ኤለን ጆንሰን ሰርለፍ፤ የአፍሪካ ሴቶች አርአያ

**ከኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) የሴቶች ኮሚቴ**

የፖለቲካው መስክ በወንዶች ክበብነት በሚታማበት ባሁኑ ወቅት አፍሪካዊቷ ሃገር ላይቤሪያ ቀዳሚ ታሪክ ሠርታና ፈር ቀዳጅ ሆና መገኘቷ ተምሳሌትነቱ ለአፍሪካውያን ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሴቶች ሁሉ ጭምር ነው።

በላይቤሪያ በቅርቡ በተደረገ አጠቃላይ ምርጫ የሃገሪቱ ሕዝብ ለኤለን ጆንሰን ሰርለፍ ከፍተኛውን የምርጫ ድምጽ በመስጠት የመጀመሪያዋ የላይቤሪያና የአፍሪካ ሴት ፕሬዘዳንት አድርጎ መሾሙ በእርግጥም የሰነበተ ዜና ይሁን እንጂ ክንዋኔው ግን ቋሚና አንፀባራቂ ታሪካዊ ድርጊት ሆኖ መቀጠሉ አይቀሬ ነው።

ሰርለፍ ቀደም ሲል በትምህርት ተቋማትና በልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ማገልገላቸው ታዋቂነትን ማስገኘት ብቻ ሳይሆን በፖለቲካውም መስክ ብቅ ሲሉ እንግዳ እንዳይሆኑ እጅጉን ረድቷቸዋል። በተለይም እስከዛሬ ድረስ የወንዶች ብቻ የነበረውን የአፍሪካውያን የፕሬዘዳንቶች ክበብ ሲቀላቀሉ የእንግድነት ስሜት እንዳይሰማቸው አግዟቸዋል። ስለዚሁ ጉዳይ ኢትዮጵያዊቷ ጋዜጠኛ መስከረም ሰርፀ ለፕሬዘዳንት ሰርለፍ ጥያቄ አቅርበውላቸው በነበረበት ወቅት ሲመልሱ“ባካዳሚው መስክና ዙሪያ ለተወሰነ ጊዜ የመቆየት ዕድል ስለነበረኝ፤ ምናልባት የእኔን በዚህ ሃላፊነት መቀመጥ ለመቀበል መጀመሪያም ሆነ ሁዋላ

ቀላል ነበር ማለት ይቻላል። ያም ሆኖ ግን አሁንም ብቸኝነት ይሰማኛል" ብለዋል።

"በአፍሪካ የመጀመሪያዋ ሴት ፕሬዘዳንት ሆኖ መመረጥ በአህጉሩ ላሉ ሴቶች ምን እገዛ ያደርጋል?" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸውም "የእኔ ፕሬዘዳንት መሆን ያፍሪካ ሴቶችን ያነቃቃል። ምክንያቱም ካሰቡት ከማንኛውም ደረጃ መድረስ እንደሚችሉ ይረዳሉና። ወጣት የላይቤሪያ ልጃገረዶች ሚኒስቴር፣ ፕሬዘዳንት፣ ወይም መሪ የመሆን ፍላጎታቸውን በግልጽ መናገር ይችላሉ። እናም ይህ በላይቤሪያ ሴቶች ዘንድ የታየ የመነቃቃት ስሜት ወደ ሌሎች ሃገሮች እንደሚዛመት ተስፋ አደርጋለሁ" ሲሉ መልሰዋል።

ፕሬዘዳንት ሰርለፍ በአፍሪካውያን ላይ ከፍተኛ የጸና ዕምነት እንዳላቸው የሚያረጋግጠው ምላሻቸው "በዓለም ካሉ ሰዎች በአርዓያነት የሚያዩት ማንን ነው?" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ሰርለፍ ስለዚህ ሲመልሱ "የታንዛኒያው የመጀመሪያው መሪ ጁልየስ ኔሬሬ በጣም የማደንቃቸው ሰው ነበሩ። ባሁኑ ወቅት ደግሞ እንደዊኒ ማንዴላና የኖቬል ሽልማት አሸናፊ የሆነችው ኬንያዊቷ ዋንጋሪ ማታይ ጥቂቶቹ ናቸው። አሁን ደግሞ ባራክ ኦባማ አሉ"፣ ሲሉ በአፍሪካውያን ወገኖቻቸው ላይ ያላቸውን ፅኑ የመተማመን ስሜት ሳይደብቁ በይፋ ገልጠው ብዙዎች ጠያቂዎቻቸውን አስደምመዋል።

ሰርለፍ እንደብዙዎቹ የአፍሪካ መሪዎች በስልጣን ለዘመናት ለመቆየት ፍላጎቱ እንደሌላቸው ለማመልከት "ላይቤሪያውያን በ2011 እ. አ. አ. እንደገና ለፕሬዘዳንትነት የመወዳደሬን ወይም አለመወዳደሬን ነገር በጉጉት እንዲጠብቁ ላደርጋቸው እፈልጋለሁ። ለጊዜው ግን ከትልቅ የልማት አጀንዳ ጋር እየታገልሁ ስለሆነ ትኩረቴ በሌሎች ነገሮች እንዲረበሽ አልፈልግም። ያሁን ትኩረቴ በዚሁ ላይ ውጤት ማስመዝገብ ነው። በስራዬ መመዘን ይኖርብኛል። የሚቀጥለው ምርጫ እ.አ.አ በ2011 ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ለመወሰን ገና ብዙ ጊዜ አለ። እሱን ለላይቤሪያ ሕዝብ እተዋለሁ" ማለታቸው ተደምጧል።

ለብዙ ጋዜጠኞች እጅግ አስገራሚ የሆነው ሌላው ምላሽ ለአፍሪካ በቀጣይነት ከምዕራባውያን ስለሚጎርፍ እርዳታ ያላቸው ለየት ያለ አመለካከት ነው። በዚህ ረገድ "አፍሪካ ያለ ዕርዳታ የተሻለ ስኬት ታገኛለች ብለው ያምናሉን?" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው "አፍሪካ ዕርዳታን በደንብ ለታቀደና ዓላማው ግልፅ ለሆነ ተግባር ልትጠቀምበት ይገባል ብዬ አምናለሁ። ያሁኑ ዋና ችግር ዕርዳታውን በአግባቡ አለመጠቀሙ ላይ ነው። ዕርዳታ ተቀባይ አገሮች የየራሳቸውንም ሃብት በደንብ መጠቀም አለባቸው። ባሁኑ ወቅት እርዳታን በአግባቡ የሚጠቀሙ በጣም ጥቂት ያፍሪካ ሃገሮች ናቸው" ሲሉ ፍርጥም ብለው የአያሌ አፍሪካ ሃገሮችን መሰረታዊ ችግር ጠቁመዋል። ብዙዎች የሰርለፍን አመለካከት በጥሞና የተከታተሉ የፖለቲካ ተንታኞች ሰርለፍ አዲሲቷ ያፍሪካ ተስፋ ሰጪ እንስት መሪ ብቻ ሳይሆኑ ለለውጥም ዝግጁ ናቸውና አርዓያነታቸው ጉልህነቱ ካድማስ ባሻገር ነው ሲሉ አወድሰዋቸዋል።

የሚገርመው እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ቀዳሚ ባለረጅም ታሪክ ሃገሮች ሕዝቦቻቸው ዛሬም በአምባገነን ገዢዎች ስር የሚማቅቁ ሆነው እንኳንስ ለሴቶች ሰፊ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ልዩ እገዛ ሊደረግ ቀርቶ ወጣ ወጣ የሚሉትንም ወደታች ለመኮርኮም የጎላ ጥረት ሲደረግ ነው የሚታየው። በቅርቡ በህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ትዕዛዝ፣ በዚሁ አገዛዝ በተሾመ ዳኛና እስር ቤት እንዲማቅቁ የተፈረደባቸው የአንድነት ፓርቲ መሪ የወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳና ሌሎችም አያሌዎች ለእስርና ለስቃይ መዳረግ ለዚህ ጉልህ ማረጋገጫ ነው።

# የወጣቶች ዓምድ

## ከፍተኛ የትምህርት ውጤት ያገኙ ወጣቶችን ምልመላ

### ከኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) የወጣቶች ኮሚቴ

ከግንቦት 20፤ 1983 ዓ/ም በሁዋላ ዓመት እየጠበቁ የሚመጡ ግንቦቶች አልፎ አልፎ ይዘውብን የሚመጡ መዘዞች እየተበራከቱ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ይህን ስንል ከምንም ተነስተን አይደለም። በቅርቡ የሃገር ቤት ጋዜጦች እንደዘገቡት ህወሃት/ኢሕአዴግ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎችን በመመልመል ላይ መሆኑን ከመጥቀሳቸውም በላይ በተለይ የአዲስ አበባ ኢሕአዴግ ጽሕፈት ቤት ከግንቦት ወር 2001 ዓ/ም እስካሁን በቀጣይነት ከየክፍሉ ከአንደኛ እስከ ሃያኛ የወጡ ተማሪዎችን በመሰብሰብ በፕላዝማ ቲቪ "ስልጠና" መስጠት መቀጠሉን ካስተማማኝ የዜና ምንጮች መረዳት ተችሏል።

ይህንን የህሊና ሰለባ ሊባልለት የሚችለውን "ስልጠና"ም የሚሰጠው ከቀበሌና ከህወሓት/ኢሕአዴግ አመራር አባላት በተውጣጡ ካድሬዎች አማካኝነት ለአራት ተከታታይ ሰዓታት ሲሆን፤ በተለይ ደግሞ ስገገርው ቡድን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሰፌ ገለፃ የሚሰጥ መሆኑ ሲታወቅ በያካባቢው የኢሕአዴግ አመራር አባላትም አማካይነት ስለ ትምህርት ጥራት፣ የተማሪዎችና የአስተማሪዎች ስነ-ምግባር ወ.ዘ.ተ ሠፊ ቅስቀሳ እየተካሄደ ያለ መሆኑም ታውቋል። በጣም የሚገርመው ደግሞ በገለጻው ሂደት አወያይ ተብዬዎች እንደ መምህርም እንደ ካድሬም እየሆኑ መሥራታቸው ሲሆን፤ ተማሪዎችን ስለህወሓት/ኢሕአዴግ ጥሩነት ማስተማር ላይ ልዩ ትኩረትእንደሚደረግም ለማወቅ ተችሏል።

ከዚህም ሌላ በሚገባ የተማሪውን አዕምሮ መበረዝ ለመቆጣጠር እንዲመች በየክፍሉ የሚመደቡ ተማሪዎች ቁጥር እጅግ አነስተኛ በአንዳንዶቹ ትምህርት ቤቶች እዚያው በግላጭና ዓይን ባወጣ ድፍረት ተማሪዎቹ የኢሕአዴግ የአባልነት ፎርም እንዲሞሉም ይደረጋል።

"የሌባ ዓይነ-ደረቅ" እንዲሉ ነውና ለምን ተማሪዎቹን ማንቃትና ማሰልጠን እንዳስፈለገም አገዛዙ በቁጥጥሩ ስር ባደረጋቸው የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ሳያፍር "ቀጣይ ሃገር ተረካቢዎች በመሆናቸው ወቅታዊ ሁኔታውን እንዲያውቁ ለማድረግ ነው" ሲል በአደባባይ ዋሽቷል። ዋነኛ አጠያያቂው ጉዳይም ይኸው ነው። የነገዋ ኢትዮጵያ ተረካቢ የሆነው ወጣት ትውልድ በትምህርት ገበታ እንዲቀርብለት ከተሰናዳ የትምህርት ዓይነት በተጨማሪ በራሱ ነፃ ሆኖ አዲስ ነገርን አፍላቂ እንዲሆን ከመገፋት ይልቅ በአገዛዙ የፖለቲካ ቅኝት እንዲሰለጥን የማስገደዱ ሁኔታ ለማናቸውም ኢትዮጵያዊ ግልጽ ከመሆኑም ባሻገር ህወሓት/ኢሕአዴግ "ለዘላለማዊ" ስልጣን ዝግጁነቱን እያሰናዳ ለመሆኑም በቂ ምስክር ነው።

በደርግ ዘመን በግድ "የፖለቲካ ንቃት" በሚል ይካሄድ የነበረውን ግርግር ይቃወም ነበር ተብሎ የሚነገርለት ህወሓት/ኢሕአዴግ ዛሬ ተረኛ ገዢ ሆኖ በሥልጣን ሲፈናጠጥ የወጣቱን ትውልድ የመደበኛ ትምህርት ሰዓት ጭምር እያባከነ የሚያደርገውን ዕኩይና ትውልድ አምካኝ ተግባር ለተመለከተ፤ ቀድሞውንም ቢሆን ተቃውሞው የይምሰል እንደነበርና ያሁኑ አጀንዳው ግን እጅጉን አሳሳቢ እንደሆነ ይረዳል። የመምህርነትንም ተግባር እየተፈታተነና እያራከሰ በመምጣቱ በዚህ ድርጊቱ በጣም እያዘኑና ሃዘናቸውንም በቁጣ እየገለጹ ያሉ መምህራን ቁጥር በመጨመር ላይ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

አንዳንድ ወገኖች ህወሓት/ኢሕአዴግ የሃገር

ተረካቢውን ወጣት ትውልድ በዚህ ዓይነቱ የአዕምሮ ብከላ ከመመረዝ ይልቅ ተግባራዊ እያደረገው ያለውን ትውልድ አምካኝ የትምህርት ፖሊሲውን ቢያርምና ቢያሻሽል ይመረጥ ነበር ሲሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ ወገኖች፤ በተለይም ተቃዋሚዎች፤ ይህንን የገገርውን ቡድን ድርጊት በመኮነን ዓላማው የአዕምሮ ብረዛና ሰለባ ነውና የኢትዮጵያ ሕዝብ በገዛ ልጆቹ ላይ የሚካሄደውን ይህን ሤራ መታገስ እንደማይኖርበትና ለመሠረታዊ ለውጥም እንዲታገል እያስተማሩ ነው።

ህወሓት/ኢሕአዴግ ባሁኑ ወቅት በተማሪዎች ላይ ብቻ ሳይሆን የምልመላ ዘመቻውን በማጠናከር በክረምት ለሚካሄዱ የትምህርት ኮርሶች በየትምህርት ማሰልጠኛው በሚሳተፉ መምህራንንም ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ወትመዱን ዘርግቶ ስለአብዮታዊ ዴሞክራሲ በግድ ኮርስ በመስጠትና የኢሕአዴግ አባልነት ደብተር እንዲወስዱም በማስገደድ ላይ ነው። ይህንን የገገርውን ቡድን ትውልድ አምካኝ ሤራ ከታሪክ አኳያ መገምገምና መፍትሔም ማመላከት የኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) እና የመሳሰሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች ግዴታና ሃላፊነት ስለሆነ ለአብነት ያህል አንዳንድ ጉዳዮችን አንስተን እንደምድም።

ትናንት፤ ማለትም በደርጉ አገዛዝ ወቅት፤ በየቀበሌውና ከዚህም አልፎ በብሔራዊ ደረጃ በተቋቋሙ በኢአ.ወማና በመሣሰሉ ድርጅቶች አማካይነት ወጣቱን ትውልድ ከፍላጎቱና ከዕምነቱ ውጭ በማስገደድና በማሰባሰብ የገገርው ቡድን ርዕዮትና ተራ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ ለማድረግ፤ ስላገሩ፤ ስለዴሞክራሲና ስለፍትህ ጉዳይ ከመሰሉ ጋር እንዳይመክር ለማገድ እንደተሞከረው ሁሉ፤ ዛሬም ህወሃት/ኢሕአዴግ ይልቁንም በሚያስከፋ መልኩ ይህንኑ ትውልድ የጎሠኝነት ሰለባ ለማድረግ ያልመከረውና ያልዘከረው ጉዳይ የለም።

ወጣቱ ትውልድ ከገገርው ቡድን ህልምና ትልም ወጣ ብሎ ለዴሞክራሲና ለፍትህ ሲቆምና ገገርውን ቡድን ባገር አንድነት፤ በዴሞክራሲ ጥያቄ፤ በፍትህ ጥያቄ ወ.ዘ.ተ ዙሪያ ከወገኑ ጋር ቆሞ መጠየቅ ሲጀምር ደግሞ በ1993 በኤርትራ ሬፈረንደምና ባለፈው የ97 ምርጫ ወቅቶች እንደታየው ሁሉ በጨካኝ በትሩ ጨፍጭፎታል።

ወጣቱ ትውልድ በኢትዮጵያ የ1960ና 70ዎቹ አብዮት ወቅት የተጫወተውን ወሳኝና መስዋዕትነትን የተላበሰ የለውጥ ሚና አገዛዙ በደንብ አድርጎ ስለሚያውቅም አሁንም ይህ ትውልድ የዚያ ዓይነቱ የለውጥ ቋያ በውስጡ እንዳይንበለበል፤ ያገኘውን አመስግኖና ገብሮም እንዲኖር ለማድረግ ከተቃዋሚው ፖለቲካ ይነጥለዋል፤ በዕለት ከዕለት ህይወቱም እየገባ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮቱ እንዲሰለብ ያደርገዋል።

የዚህ ዓይነቱን የአዕምሮ ሰለባ፤ በእንግሊዝኛው አጠራር ዴማጎጂ፤ በአንድ ሕዝብ ላይ፤ በተለይም በወጣቱ ትውልድ ላይ፤ ያሳደረውን አሉታዊ ዕውነታ ከታሪክ ማህደር ስናገላብጥ የጎብልስን የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳና የሂትለርን የናዚ ፓርቲ ዕድገት፤ ከዚያም ጥፋቱንና የጀርመንን ህዝብ እፍረትና ውርደት ያሳየናል። ፓርቲው ጠፋ፤ ሕዝቡ ግን ወንጀል በትውልድ እንደማይተላለፍ ቢያምንም፤ እስካሁን ግን ከሚነገርለት ውርደቱ ጋር ይኖራል። ከዚህም ብዙ መማር ተገቢ ይመስለናል።

ስለዚህም ወጣቱ ትውልድ የጀርመኑ ትውልድ ዓይነት የቅጥፈት ሰለባ እንዳይሆን ይህንን መሠሪ የህወሓት/ኢሕአዴግ ሤራ እንዲዋጋና ለዴሞክራሲና ለፍትህ የሚደረገው ትግልም አካል እንዲሆን ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

# ከሥነፅሁፍ አምባ

## ምርጫ

ዓመት ሰፍሮ ቀን ቆጥሮ፤
ውሸት አንግሶ እውነት ቀብሮ፤
መጣ ደግሞ ምርጫ፤
የፋሲካ ደም መርጫ።
ሊጭን ቀንበር ሊያስር ማነቆ፤
ሞት አውጆ ስደት ሰንቆ፤
ሊያራጭ ዕንባ ቤት ሊያዘጋ፤
ሰው ሊያጋድል ሰው ሊያዋጋ።

እያለቅን ከመቸገር፤
ምርጫ ቢቀር ይሻል ነበር፤
እባክህ ቅር ምርጫ አትምጣ፤
ደም የለንም የሚጠጣ።
በእኩለ ቀን ግንቦት ስባት፤
ገብረናል ብዙ ወጣት፤
ሞት ደግሰህ ምሳር ስለህ፤
አትደልለን ምርጫ ብለህ።

መች ተረሳ የትላንቱ፤
አይበቃም ወይ የግንቦቱ፤
የፈሰሰው ደም በከንቱ፤
የሕፃን የወጣት ያዛውንቱ፤

የወደቀው ሳያገግም ሳይሄድ ቆሞ፤
ምን ልትሰራ መጣህ ደግሞ?
አመርቅዞ ገና ሳይሽር ቁስላችን፤
ሳይረሳ ሀዘናችን፤
ስብራቱ ሳይጠገን የልባችን፤
መጣህ ደግሞ ልትቆሰቁስ፤
ልታያይዝ ልታላኩስ ፤
ከሚሰብኩ ብለው ምርጫ፤
የፍትሕ በር መግቢያ መውጫ፤
ባይጠራ ሥምህ ጭራሽ፤
ይሻል ነበር ብትሞትና ቢቆም
አልቃሽ።

ምን ጠቀመን ያንተ መኖር፤
ቢያወድሱህ በላይ ሰፈር፤
ሞት ሰንቀህ አሽምቀህ፤
አንገት ደፊ ገራም መስለህ ፤
ያንን አስረህ ይህን ገድለህ፤
አባቱ ፊት ልጁን ደፍተህ፤
አስለቀስህ እንባ አራጭተህ፤
መጣህ ምርጫ ዓመት ቆጥረህ።

ለማን ዳኛ አቤት እንበል…
እንዳትመጣ ሰፈራችን
እንዳናይህ በዓይናችን…
እንዳትነግድ በስማችን፤
ሕግ ቢኖር ሰው የሚዳኝ
ትላክ ነበር ዓለም-በቃኝ ።

ህወሓትን ተሸክመህ፤
"አጋሮቹን" አስከትልህ፤
እባብ ሆነህ ርግብ መስለህ፤
ወግተህ ልትገድል እንደያኔው፤
እንደ ግንቦት እንደሰኔው ፤
መጣህ ምርጫ ሞት ደግሰህ፤
ልትቀብር መሬት ምሰህ፤
ቤት አፍርሰህ እናቶችን አስለቅሰህ፤
ማር ቁረጡ ጣፋጭ ነኝ ብለህ፤
በቀፎ ውስጥ ተርብ አኑረህ፤
ስንቱን መረዝክ ነድፈህ ነክሰህ።

ተሸክመህ ያኖርከውን፤
ወያኔውን ያዘልከውን፤
አውርድና ከጀርባህ ላይ፤
እንወያይ ባገር ጉዳይ፤
ቀና ብለህ አትሂድ፤
ቋንጃህ ታስሮ አትራመድ፤
በድን ይዘን ከምንፎክር፤
ይሻለናል አፈር ለብሰህ ብትቀር፤
ጆሮ የለህ አትሰማ፤ ምላስ የለህ
አትናገር፤
ምርጫ ብለን ስንት ዘመን እንቸገር፤
የጨካኝ ሰው ወዳጅ ሆነህ፤
ሺውን ገድልህ ሺውን አስረህ፤
ደም አዙሮህ በደም ሰክርህ፤
ዳግም መጣህ ሐፍረት የለህ!!

ምርጫ ስማኝ፤
ቃል ግባልኝ፤
ላልክድህ ላትከዳኝ፤
ላልተውህ ላትተወኝ፤
ቃል ግባልኝ፤
ጡንቸኛ ወንበዴ ሕግ የማይገዛውን፤
በስምህ ደልሎ የሚነግደውን፤
አጋልጠህ ወዲያ ወርውረህ ጣልና፤
ሕዝብ የወለደውን ኢ.ሕ.አ.ፓን ይዘህ
ና።

ለፈሰሰውም ደም ዋጋ
የምትከፍለው፤
ይህ ሲሆን ብቻ ነው የምንታረቀው ፤

ምርጫ…

ወያኔን ሰውረህ በጉያህ ሸጉጠህ
ብትመጣ መንደሬ ዓይንህን
አፍጥጠህ፤
ስምህን ላልጠራ ቃል ለምድር ለሰማይ
ዓይንህንም ላላይ የኔንም ዓይን
ላታይ።
ቀን እስኪወጣልን ጎድን አልንህ
ምርጫ፤
በስምህ ከምናልቅ በወያኔ ጡጫ፤
ዳግም እንዳትመጣ እባክህ ቅር
ምርጫ፤
ይብቃ እንዳይደገም የግንቦት ሰባቱ
ለይስሙላ ምርጫ መታሰር መሞቱ።

(ከዳዲሞስ)

……//……

## ምሥጋናና ማሳሰቢያ

ከሁሉ አስቀድሞ በዚህ የዜና መጽሔታችን የወጡትንና ድርጅት ነክ ያልሆኑ ጽሁፎችን ለላኩልን ግለሰቦች ሁሉ በኢ.ሕ.አ.ፓ (ዴሞክራሲያዊ) ስም ከፍተኛ ምሥጋናችንን እናቀርባለን።
እነዚህን ጽሁፎች ለንባብ እንዲመቹ አንዳንድ የፊደል ግድፈቶችን ከማረምና ከማስተካከል ውጭ የጸሐፊዎቹን መብት ላለመጋፋት ስንል ጽሁፎቹ ያዘሏቸውን መልዕክቶችም ሆነ ደራሲዎቹ የተጠቀሙባቸውን ጽንሰ-ሃሳቦች እንዳሉ አውጥተናል፤ እናወጣለንም። ይሁንና በነዚህ ጽሁፎች ዙሪያ ግድፈት ወይም ሌላ የሚያስጠይቅ ጉዳይ ካለ፤ ይህ የድርጅታችን ኦፊሴላዊ አቋም እንዳልሆነ አንባቢያን እንዲረዱልን በትህትና እናሳስባለን።

የዜና ኢ.ሕ.አ.ፓ ዝግጅት ክፍል

# Book Review

**Book Title: *"The Ethiopian Revolution" - War In The Horn of Africa***

**Author: Gebru Tareke (Prof.)**

**Year Published : 2009**

**Publishing House : Yale University Press**

**Pages: 437**

**Reviewed By: Mulu Gebeyehu**

Gebru is emeritus history professor with 31 years of teaching at Hobart and Smith Colleges. Initially, Gebru titled his book "*Comrades Against Comrades -The Ethiopians in Revolution and War"*. However, perhaps sensing that he had already authored a few years ago a piece on the same theme, *"The Red Terror in Ethiopia - A Historical Aberration*[1]*"*, Gebru settled on the current title for his seminal book. Still, the provisional title was kept and made the title of Part 2 of this new book. Perhaps his better known previous work is "Ethiopia: Power and Protest: Peasant Revolt in the 20th Century" (Journal of Developing Societies, pp.183-206, vol.24 #2 1996).

This review is divided into 3 sections. In the first part, we will show that Gebru is a progressive Ethiopianist hailing from Tigrai, and not a Tigrean parochialist as some would hastily and erroneously conclude. This will be followed by his analysis of the EPRP and a conclusion.

Gebru dedicates his book to the memory of his parents and kindly to "all those who died for a free, democratic, and secular Ethiopia" .

## Gebru: Progressive Ethiopianist

In a political era where some amateurs are engaged in the pernicious perfidy of the indiscriminate criminalizing of Tigreans, it is imperative to debunk their ignorance by citing examples of Tigreans in the era of the TPLF that have steadfastly stood fordemocracy, Ethiopiawinet and the rule of law. Prof. Gebru is one such Ethiopian.

Gebru seems to have spent well over a decade working on this book. He traveled to Ethiopia in 1994 and interviewed over 500 people from all spectrums, except as regretfully admitted by him his failure to get the cooperation of the Eritrean side. He also got access to the treasure of the Ministry of National Defenses' documents which he profusely and liberally referenced in the book.

From the outset, in an uncharacteristic frank admission, Gebru honestly pleads guilt on his inability to stay neutral in the interpretation of such momentous events. However, he assures us that he has made a special effort to keep his biases to a minimum (p.xiv), and it seems to me that he has succeeded beyond expectations in spite of his fleeting reference that he may have once belonged to EPRP (p.79) - not that every one that once belonged to EPRP now has charitable and kind words for the organization.

Discussing the relationship between TPLF and the people of Tigray, he states "...but not everything they did [i.e. TPLF] was spontaneous or of their own free will. There was a lot of manipulation and coercion involved. Partly through inducements and partly by intimidation, the front mobilized thousands..."(p.108). This objective assessment of TPLF, among others, earned him the wrath of General Tsadkan -one of his reviewers- as

we shall see later. In a similar vein, on page 76, the author says: "another fraud has been perpetrated by a segment of Tigrean "modern ‘elite that ascribes the territory's poverty to "successive Shoan rulers'.

The best antidote to such hoaxes is history. Do, “let's begin." With that, he smoothly sails into correcting the record.

Among the malevolent assistants of Mengistu, Gebru mentions the notorious Corporal GabreHiwot Gebre Egziabher (p.44) who was posthumously known to have infiltrated the Derg for TPLF and who along with Melaku Tefera (the butcher of Gondar) decimated thousands of youth in central and northern Gondar.

The author also ridicules one of the Derg’s luminaries, Major Fisseha Desta who at one time uttered male chauvinistic remarks and Gebru puzzles by saying "this after 16 years of communistic rhetoric (p.379/23).

While analyzing the Derg's resettlement program, Gebru's progressive probity shows with full force. While it has been commonplace to disparage the program just to score political points against the Derg, Gebru dispassionately analyzes the resettlement program as a socio-economic imperative and casts aside the unsupported criticisms, such as the ones made by Major Dawit W/Giorgis in his book "*Red Tears"*, and the rebels who shrilly argued that the Derg's motive was to depopulate Tigray.

The author rests his case on this issue by mentioning the fact that TPLF has now embraced resettlement as one solution to the pressing problem of ecological degradation and rural poverty, but wonders how in the era of "ethnic states" this would be implemented (p.380/26).

Commenting on a similar event, the famine of 1985 and TPLF's actions, he says: "The TPLF went further to convince the international community by forcing the thousands of people under its control to emigrate to the Sudan. Claiming that it had only facilitated their exit to save them from the claws of a" genocidal regime", it paraded many of the ragged peasants before the international media. It was an unpleasant spectacle but may have achieved its intended purpose of shaming the regime"(p.380/34) -see also Gebremedhin Araya's, a former TPLF official, recent postings on **Ethiomedia** for detailed and serialized information on this particular subject.

Turning to his profession - education, Gebru laments at the tens of thousands of ill-educated and ill-equipped young Ethiopians. He partly attributes the national crisis to the fact that all the leaders of state universities are political appointees (he says this without naming Endrias Eshete - so self-evident, it was probably not necessary).

"Despite two revolutions, there still is not a single chartered autonomous institution of higher learning and should be a national disgrace" says Gebru (p.336).

Gebru also pays attention to a little-discussed tragedy in contemporary Ethiopia, i.e. the sad fate of the disbanded Ethiopian soldiers who lost the war to TPLF.

Through his interviews, one senses the palpable anger and destitution of these heroes who have been thrown out to their devices as if they have not heroically served their nation. Gebru's narration of a chance meeting with a 20 year old former soldier-turned-shoeshine is revealing. Asked by Gebru how he feels about the peace that the country has achieved since TPLF's assumption of power, the youth replies :"sir, what good is peace without bread and water?"(p.122). The author reminds the nation to kick start a national reconciliation program, one of whose acts could be the erection of a memorial for all Ethiopians who lost their lives fighting on different sides of the cleavage (p.323).

One of the two TPLF generals that Gebru admires is Hayelom Araya (the other being

"the first 4-star Ethiopian Moslem general" Samora Yunus). While Hayelom's rise to military prominence is admirable as an individual accomplishment, his interview with the author belies TPLF's narrow nationalism. Asked by the author who he admired of his Derg opponent officers, Hayelom mentions only two commanders who have Tigrean sounding names serving under the Ethiopian army: Col. Sereke Berhan, about whose bravery at least the author tells us, and a Brigadier General Araya Zeraay, about whom nothing is recorded in a 437 page book (p.367/62). This is how ethnicized politics defiles the body politic of a country.

As I was admiring the diligence of the author in sifting through the Ministry of Defense documents and interviewing no less than 500 including former and current army officers, one question kept coming to my mind. Would this access to government documents and personnel have been possibly granted by TPLF to a non-Tigrean Ethiopian historian, such as Bahiru Zewdie or Teshale Tibebu, or Shumet Sishagne?

## On The EPRP

To his credit, Gebru, while discussing the atrocities perpetrated against the youthful radical generation of the 1970's, does not use the fictive "White Terror" appellation that Derg apologists have thrown in the political lexicon. Instead, he puts the crimes fittingly under the rubric of the Derg's Red Terror. EPRP was neither a government nor a power symmetrical with the Derg to conduct a counterattack. What it engaged in was a limited self-defense that quickly crumbled in the face of massive atrocity meted out by the Derg.

Discussing the TPLF versus EPRP disagreements and eventual war in Tigray (PP.87-88), Gebru displays extreme caution to a fault. Gebru could have mentioned the "Abay Ethiopia" 'pejorative' term TPLF lashed out at EPRP. He could have also mentioned the insult Tigrean EPRPites endured while being called "korakur Amhara" (puppets of the Amharas) by the TPLF.

This was the TPLF that was burning with narrow Tigrean nationalism and regarded EPRP politically as its existential threat and did everything from repeated provocative acts to harassing its mass organizations, such as peasant associations before it opened a full war against it.

And unashamedly, TPLF's Major General Tsadikan tells a white lie in his review of Gebru's book that EPRP was forced out of Tigray as a result of the local peoples decision/ referenda in Golomakeda, and Erob. TPLF was driven into desperation and war when the Tigrean broad peasants and intellectuals rejected its narrow nationalism and toying with the notion of secession. What proof to cite for EPRP other than the live and continuing exhibit of TPLF’s own narrow nationalist agenda that has been plaguing the nation for almost two decades. Tsadikan goes on to heaping praise on EPDM for staying put in the field when the rest fled to the West.

It is small wonder that Tsdaikan puts the EPDM in a positive light, an outfit that made a Faustian bargain with the TPLF as an enabler for the latter to get a cover as an Ethiopianist force. Soon after its Addis Abeba entry, EPDM was molded into an "Amhara Democratic Movement (ANDM)" dropping its former name and identity. So much for Tsadkan’s rhetoric claim of staying put in the field.

Likewise, Gebru could have done a comparative analysis of the positions of EPRP and TPLF on the Eritrean question. Although the two organizations might have shared the secession right of Eritreans, for TPLF this derived from the colonial thesis it ascribed in the Ethio-Eritrean relation, while for EPRP

the Eritrean question fell in the broad category of the National Question, and hence secession might not be the only and even the most desirable option. In line with its colonial thesis and to help Eritrea achieve its “liberty”, by the freewheeling admission of General Tsdaikan, TPLF has sent up to 5,000 fighters to the Eritreans aid, and the favor was returned by the Eritreans during TPLF's Shire engagements with the Derg. With times now changed, Tsadikan puts down the Eritreans as a military power and a former protégé.

To set the historical record straight, in order to resolve the problem it had with TPLF, the EPRP proposed 3 solutions: 1) working in a united front where other entities might also be members of the front; 2) a full merger and 3) a "live and let live" policy for each organization respecting their separate operations free of provocations. But the TPLF's insistent demand was for EPRP to evacuate Tigray.

Turning to EPRP's relations with the Derg, the author brings out a common myth and lie that was and remains to be a cruel protégé.This is the allegation that EPRP had assisted Somalia in its war with Ethiopia, or in its mildest form, that the EPRP had sabotaged Ethiopia's effort to crush the Somali invasion. Practically, any soldier or officer associated with the Derg and who has written a book, with the possible exception of General Tesfaye Habtemariam, has indulged in this escape-goating enterprise. This list includes B/General Kassaye Chemeda, a Derg general who also reviewed Gebru's book. Curiously, not one of them has produced a shred of evidence to support this allegation. It seems that because EPRP was the leading opponent of the dictatorial Derg at that time, any legitimate grievance or concern by any Ethiopian in the military or in civilian discourse was attributed to EPRP. So, for any losses the Derg suffered in the Ogaden Front, or for any challenges and suggestions that came from the units on the ground, the proponents were categorized as EPRP and summarily executed (p.198). Later after the Derg crushed EPRP's urban structures and yet the challenges and alternative thoughts flourished around the various war fronts, such as Naqfa, Shire and Massawa, there was no EPRP to blame.

Instead of taking full responsibility for its mistaken policies and the subsequent disasters such policies resulted in and instead of facilitating the establishment of a Provisional People's Government as EPRP steadfastly called, Mengistu went on a rampage of murdering irreplaceable officers and NCOs among its ranks.

## Conclusion

Gebru has written a superb book supported by a rich and verifiable data. The data pertains to the type and number of equipment the combatants used, the forces arrayed, the desertions, the war victims and the expenditures. For proper context, he also provides an overview of the struggles [winners and losers] of several guerrilla movements across the globe including that of Nicaragua, Mozambique, Kenya, the Boers, Uganda, Rwanda, Algeria, Malaysia and Guatemala. He occasionally compared the Ethiopian revolution with that of Iran, and the Ethio-Somali war of 1977-78 with that of the 8 year Iran-Iraq war beginning in 1980.

Gebru has made a crucial contribution to the study of Ethiopian history and politics and he must be applauded for this incredible work.

……//……

**HISTORY IS BEST TOLD BY THOSE WHO WERE PART OF ITS MAKING & GEBRU TAREKE WAS IN IT!**

**ለሰማዕታት ጓዶቻችን የምናበራው ሻማ ለነርሱ ያለን ዘልዓለማዊ ፍቅርና የ ሃዘናችን መግለጫ እንዲሁም ለጀግንነታቸው የምንጊዜም ማስታወሻ ነው!!!**



**"ምርጫ እኮ ጥሩ ነው፤ ጥሩ ነው ምርጫማ፤
ድምፃችን ተሠርቋል ካላላችሁማ።
ከቶ የት ይገኛል? ምርጫን የመሰለ፤
ከውስጥም ከውጭም ታዛቢ ከሌለ።
ተቃዋሚ ፓርቲ ጠፍቶልን ካገሩ፤
ቢሆን ጽቡቅ ነበር ምርጫ በየወሩ።
ምርጫ እኮ ጥሩ ነው ክብሩም የገነነ፤
ምርጫ አስፈፃሚው የራስ ሰው ከሆነ።
እንደምርጫ አስደሳች የት ይገኛል እስቲ፤
በተለይ ከሌለ ተቃዋሚ ፓርቲ።"**

**(በአንድነት የእራት ምሽት ላይ የተነበበና ሸበላው ከአውሮፓ ባንዱ ፅሁፋቸው የጠቀሱት ከኢትዮ ሚዲያ ድረ-ገጽ የተገኘ)**

**ከምርጫም ከድርድርም በፊት የተቃዋሚዎች በህብረት መቆምና በጋራና በተቀነባበረ ትግል ህወሓት/ ኢሕአዴግን ለመጣል የሚያስችል የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ ሊኖር የግድ ነው። በነጠላ ድርድርም ሆነ ምርጫ ትርፉ ውድቀትና የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍዳና መከራ ማራዘም ነው!!!**

## <u>ለምትጽፉልን ወይም ለምትደውሉልን አድራሻችን</u>


**EPRP (Democratic)
850 Sligo Avenue, Suite # 8
Silver Spring MD 20877**

**EPRP (Democratic)
P. O . Box 88675
Los Angeles CA 90009**

**EPRP (Democratic)
P. O. Box 8141
Silver Spring MD 20910**

**mail: Emailtoeprp@aol.com**

**Telephone:- 301-578-4466
301-578-4465
Fax: 202-449-8363**